 የቀን ጎዶሎ

ገጽ 10

ያልጎበጡ
ትከሻዎች ...

ገጽ 17

የምርጫ ዓመት
የወረት "ፍካት"

ገጽ 18


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

83ኛ ዓመት ቁጥር 012 መስከረም 12 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## "ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሥራ መፍጠር ያስችላል"

- እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ



**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ሁለተኛው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ መወዳደር የሚችል ሥራ ፈጣሪ ማኅበረሰብ መፍጠር ያስችላል ሲሉ የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታው እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር) ገለጹ።


ሚኒስትር ዴኤታው እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር) ሁለተኛውን ሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ አስመልክተው በሰጡት ማብራሪያ የመጀመሪያው ሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ በጥልቀት ከተገመገመ በኋላ ሁለተኛ ምዕራፍ መጀመሩን አስታውቀዋል።

በሁለተኛው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ተወዳዳሪ የሥራ ፈጠራ፣ የምግብ ዋስትና ማረጋገጥና ምርትና ማርታማነትን ማሳደግ የትኩረት አቅጣጫ ይሆናሉ ብለዋል።

የኢኮኖሚ ማሻሻያው የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎችን በማነቃቃትና የዕድገት ምንጮቻችንን በማስፋት ንቁና ተወዳዳሪ፣ የሀገር ውስጥ ኢንተርፕራይዝ ለመፍጠር ይሠራል ሲሉ ተናግረዋል።

በመጀመሪያው ዙር የኢኮኖሚ ማሻሻያ በሴክተሮች የማምረት አቅም ላይ በሰፊው ትኩረት በመስጠት ተሠርቷል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በአሁኑ ያገለገሉ ሥራ ፈጣሪዎቻችንን አቅም በማየት የማሳደግ ሥራዎች ይሠራሉ ብለዋል።

"ሀገር በቀል የኢኮናሚ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል













## ኢትዮጵያ በ78ኛው የተመድ ጠቅላላ ጉባዔ ስኬታማ የዲፕሎማሲ ሥራ እያከናወነች ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በ78ኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ ስኬታማ የዲፕሎማሲ ሥራ እያከናወነች መሆኑን በተመድ የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ አምባሳደር ተስፋዬ ይልማ አስታወቁ።

78ኛው የተመድ ጠቅላላ ጉባዔ "ሰላም፣ ብልጽግና፣ ለውጥና ዘላቂነት" በሚል መሪ ሃሳብ በአሜሪካ ኒውዮርክ

ኢትዮጵያ በ78ኛው ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

## "የባሕልና የኃይማኖት ልዩነቶቻችንን ወደ እድል መቀየር ይገባል"

- አቶ ቀጀላ መርዳሳ
የባህልና ስፖርት ሚኒስትር

**ዋቅሹም ፍቃዱ**



አዲስ አበባ፡- የሀገሪቱን የባሕልና የኃይማኖት ልዩነት ወደ እድል በመቀየር ተጠቃሚ መሆን እንደሚገባ የባሕልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጀላ መርዳሳ አስታወቁ። ልዩነቱን ውበትና የኢኮሚኖሚ ምንጭ ለማድረግ የፊልም ፖሊሲ ተቀርጾ መዋቅር እየተዘረጋ መሆኑንም አንስተዋል።

አቶ ቀጀላ የዘንድሮ መስቀል፣የመውሊድና የእሬቻ በዓላትን አስመልክቶ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ከኢትዮጵያ ጋር ተቀራራቢ የኃይማኖት፣ የቋንቋና የባሕል ብዝሃነት ያላቸው እንደ ህንድ ያሉ የዓለም ሀገሮች ልዩነቱን ወደ እድል በመቀየር በተለይ በፊልም ኢንዱስትሪ በርካታ ገንዘብ እያመነጩ ነው። ከዚህ አንጻር በኢትዮጵያም የተለያዩ በዓላት ሲከበሩ አንድነትንና ወንድማማችነትን ከማጠናከር በዘለለ ወደ ዘላቂ ጥቅሞች ለማሸጋገር በትኩረት እየተሠራ ይገኛል።

ቀደም ሲል የተለያዩ ባሕላዊና ኃይማኖታዊ በዓላት ሲከበሩ ፖለቲከኞች እንደ እድል ተጠቅመው

"የባሕልና የኃይማኖት ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል






## ኢትዮጵያና አልጀሪያ ግንኙነታቸውን ለማሳደግ በጋራ እየሠሩ ነው

- ከአልጀርስ ወደ አዲስ አበባ ቀጥታ በረራ ተጀምሯል

ገጽ 8








# ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን የመከላከል ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል

## - ከ11 ሺህ በላይ ቀበሌዎች ላይ ግንዛቤ ተፈጥሯል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን በዘላቂነት የመከላከልና ለማህበረሰቡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ተግባር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በተጠናቀቀው 2015 በጀት ዓመት ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር በብዛት በሚፈጸምባቸው ከ11 ሺህ በላይ ቀበሌዎች ላይ ግንዛቤ መፍጠር መቻሉ ተጠቁሟል።

የሕገወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከልና የተመላሽ ዜጎች ድጋፍና ክትትል መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ደረጀ ተግይበሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሕገወጥ ስደትን በዘላቂነት ለመከላከል ለአምስት ዓመት የሚተገበር የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶ እየተሠራ ይገኛል።

ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ባህል ተደርጎ የሚፈጸምባቸው አካባቢዎችን በመለየት ሕገ-ወጥ ስደትን ለመከላከል ለማህበረሰቡ ግንዛቤ የመፍጠር፣ የመጠበቅ እና የመከላከል ሥራ እየተሠራ ሲሆን፤ በቀጣይም ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

እንደ አቶ ደረጀ ገለጻ፣ በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች ሕገ-ወጥ ስደት ባህልና የሥራ አማራጭ ተደርጎ እየተወሰደ ይገኛል። በዚህም ወላጆች፣ የሃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች ወደተለያዩ ሀገራት በሕገወጥ መንገድ ልጆቻቸውን መርቀው ሲልኩ ይስተዋላል ሲሉ ተናግረዋል።

ይህንን አስተሳሰብ ለመቀየር ማህበረሰቡ ላይ መሥራት ተገቢ በመሆኑ ከቀበሌ ጀምሮ በሁሉም መዋቅር ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ የመፍጠር፣ ከስደት ተመላሾች ተመልሰው እንዳይሄዱ የማድረግ፤ እንዲሁም በስደት ላይ የሚገኙ ዜጎችን መብትና ደህንነት የማስጠበቅ፣ በአስቸጋሪ ሁኔታ የሚገኙትን የማስመለስ፣ ወደ ሀገር ሲገቡ ተገቢውን ማህበራዊ አገልግሎት እንዲያገኙ የማድረግ እና ሕገወጥ ስደትን በዘላቂነት የመከላከል ተግባር እየተሠራ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።



ፎቶ፦ ገባቦ ገብሬ

አቶ ደረጀ ተግይበሉ

ከሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት ጋር በጋራ በመሆን ሕገ-ወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች ላይ ርምጃ የመውሰድ፣ በሕገወጥ መንገድ የሚዘዋወሩ ንብረቶችን የመውረስ እና ሌሎች ተግባራት እየተሠሩ ነው ያሉት አቶ ደረጀ፤ በ2015 በጀት ዓመት በቀድሞው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል 153 እና በአዲስ አበባ ከተማ 170 የሚጠጉ ሕገ-ወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች (ደላላዎች) ተይዘው ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እየታየ መሆኑን ገልጸዋል።

በሌሎች ክልሎችም በሚመለከተው አካል ርምጃ የተወሰደባቸው እና ጉዳያቸው በሂደት ላይ የሚገኝ በርካታ አዘዋዋሪዎች መኖራቸውን ገልጸው፤ ዜጎችን በሕገወጥ መንገድ የሚያዘዋውሩ ደላላዎች ከአንዱ ሀገር እስከሌላኛው ሀገር ድረስ የተሳሰሩ በመሆናቸው ኢትዮጵያውያንና ዓለምአቀፍ አዘዋዋሪዎችን ከሌሎች ሀገራት ጋር በመተባበር በሚመለከተው አካላት ርምጃ እንዲወሰድባቸው የማድረግ ተግባር ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

ዜጎች ሕገወጥ ስደትን አቁመው በሀገር ውስጥ ባለ የሥራ አማራጮች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን እና ሕጋዊ መንገድን ተከትለው በውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት ተጠቃሚ ለመሆን በርካታ ወጣቶች ከሚሄዱባቸው ሀገራት ጋር በትብብር ለመሥራት መታቀዱን ተናግረዋል።

በተጠናቀቀው 2015 በጀት ዓመት ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር በብዛት በሚፈጸምባቸው ከ11 ሺህ በላይ ቀበሌዎች ላይ ግንዛቤ ተፈጥሯል ያሉት አቶ ደረጀ፤ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን የመከላከልና ለህብረተሰቡ ግንዛቤ የመፍጠር ተግባራት በቀጣይም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወጣት በሕገወጥ መንገድ በሚሰደድባቸው በአማራ፣ በኦሮሚያ እና በቀድሞው የደቡብ ክልሎች ላይ ቀበሌ ድረስ በመውረድ የሚሰደዱበትን ምክንያት እና የማህበረሰቡን አመለካከት መቀየር የሚያስችል ግንዛቤ መፈጠሩን ገልጸዋል።



አቶ ታምራት ደምሴ

# የክልሉን የማእድን ጥናት ለማሳለጥ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር እየተሠራ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የክልሉን የማእድን ሀብት ለማወቅ የሚደረገውን ጥናት የተሳለጠ ለማድረግ በክልሉ ከሚገኙ 10 ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በጋራ እየሠራ መሆኑን የአማራ ክልል የማእድን ሀብት ልማት ቢሮ ገለጸ፡፡

በአማራ ክልል የማእድን ሀብት ልማት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ታምራት ደምሴ፤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤ በክልሉ የሚገኙትን ማእድናት በስፋት ለማወቅ የሚደረገውን ጥናት የተሳለጠ ለማድረግ ቢሮው በክልሉ ከሚገኙ 10 ዩኒቨርሲቲዎች ጋር እየሠራ ይገኛል፡፡

በክልሉ የማእድን ሀብት ጥናት 70 ከመቶ የሚሆነው አካባቢ እንዳልተጠና የተናገሩት ምክትል ኃላፊው ፤ የአካባቢውን የማእድን ክምችት የበለጠ ለማወቅ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር መሥራት አስፈላጊ መሆኑን አንስተዋል፡፡

በጋራ ለመሥራት የተመረጡ የኒቨርሲቲዎች የማእድን ጥናት ለማካሄድ የሚያገለግል መሣሪያ እና የሥነ ምድር ትምህርት ክፍል ያላቸው እንደሆኑ ተናግረዋል፡፡

ጎንደር፤ ባህርዳር፤ ወሎ፤ ደብረብርሃን እና ወልዲያ የኒቨርሲቲ ጥናት ወደማድረግ የገቡ ሲሆን፤ በዘንድሮ በጀት ዓመት መቅደላ፤ እንጂባራ እና ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ወደ ሥራ የሚገቡ ይሆናል ሲሉ አስረድተዋል።

አቶ ታምራት እንደገለጹት፤ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት ዩኒቨርሲቲዎቹ በዋናነት ሶስት ሥራዎችን ይሠራሉ፡፡

የመጀመሪያው ዩኒቨርሲቲዎቹ በሚገኙበት አካባቢ የሚገኙትን ማእድናት በማጥናት፤ ካርታ በመሥራት በአካባቢው የሚገኙትን ማእድናት ማወቅ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በ2015 በጀት ዓመት በዩኒቨርሲቲዎቹ ከ10 ሺህ ካሬ ኪሎ ሜትር በላይ መሬት ማጥናት ችሏል። ይህም ከተቀመጠው እቅድ 90 ከመቶ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

እንደ ምክትል ኃላፊው ንግግር ሁለተኛው የዩኒቨርሲቲዎቹ ሥራ ጥናት ከተደረገ በኋላ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡትን ፤ ከውጪ ሀገራት የሚገቡ ማእድናትን መተካት የሚችሉ ማእድናትን ጨምሮ የማእድናቱን ከምችት መጠን እና ጥራት መለየት ነው፡፡

ሌላኛው የአቅም ግንባታ ሥራ ሲሆን ፤ በዚህም ለማእድን ቢሮው ባለሙያዎች ሥልጠናን ጨምሮ የቴክኖሎጂ ክፍተትን የሚሞሉ ድጋፎችን ማድረግ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

የማእድን ቢሮው ባሉት ባለሙያዎች እና የበጀት አቅም በክልሉ የሚገኙትን ሁሉንም አካባቢዎች ማጥናት አስቸጋሪ ነው ያሉት ምክትል ኃላፊው፤ በጋራ መሥራቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በክልሉ የሚገኙትን ማእድናት ለማወቅ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል፡፡

ከዩኒቨርሲቲዎቹ የሚመረቁ ተማሪዎች የመመረቂያ ፅሁፋቸውን በአካባቢው በሚገኙ ማእድናት ላይ እንዲሠሩ ትልቅ እድልን ይፈጥራል። ይህም ለማእድን ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር አክለው ገልጸዋል፡፡

በዘንድሮው በጀት ዓመት በዩኒቨርሲቲዎቹ 20 ሺህ ካሬ ኪሎ ሜትር የሚጠጋ መሬት ለማስጠናት እቅድ እንደያዘም ጠቅሰዋል፡፡

በመጨረሻም ከማእድን ሚኒስቴር በኩል እየተደረገ ለሚገኘው ድጋፍ እና የክልሉ ነዋሪዎች በአካባቢው የሚገኙ ማእድናት እንዲጠኑ ለሚያደርጉት ድጋፍ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

# የጌዲዮ ዞን መልክአምድር በዓለም ቅርስነት መመዝገቡ በዞኑ የቱሪስት ፍሰት እንዲጨምር ያደርጋል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የጌዲዮ ዞን መልከአምድር አቀማመጥ በዓለም ቅርስነት መመዝገቡ በዞኑ የቱሪስት ፍሰት እንዲጨምር በማድረግ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኝ መሆኑን የጌዲዮ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ገለጸ። በዞኑ ያሉ የቱሪስት መስህቦችን በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ እየተሠራ ነው፡፡

የጌዲዮ ዞን ባህልና ቱሪዝም የኮሙዩኒኬሽንና ኢንፎርሜሽን ባለሙያ አቶ ዳንኤል ከተማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዞኑ ቀደምት አባቶች በሀገር በቀል እውቀታቸው በመጠቀም ከጥንት ጀምሮ ይዞት የቆየው የመሬት አያያዝ የደንና የቅርሶች አጠባበቅ፤ ከአምስት ሺ ዓመታት በላይ ተንከባክበው ያቆዩት አኩሪ ታሪክ ነው። የዞኑ ህዝብ ከጥንት ጀምሮ ዛፍን ያለመቁረጥ፣ አንድ ሲቆርጡ በምትኩ ሁለት ዛፍ የመትከል ልምድና ባህል አለው፡፡

እንደ አቶ ዳንኤል ገለጻ፤ በደራሮ በሚከናወነው ዓመታዊ በዓል ላይ ደን እንዳይቆረጥ፤ ልማት እንዲስፋፋ፣ በየአካባቢው ያሉ ሀገር በቀል ዕውቀቶች እንዲዳብሩና ባህሉ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አዋጅ ይተላለፋል። ህዝቡ አዋጁን ተቀብሎ ወደ ተግባር የመለወጥ ልምድ ያዳበረ ነው፡፡

በዞኑ በርካታ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ፣ ባህላዊ ቅርሶችን የቱሪስት መዳረሻዎችና መስህቦች እንደሚገኙ የገለጹት የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያው፤ መስህቦቹ በስፋት እንዲታወቁ ዞኑ ከክልለና ከፌዴራል ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በቁርጠኝነት ሰርቷል። በምስራቅ አፍሪካ 10 ሺ ትክል ድንጋዮች ይገኛሉ ተብሎ ከሚጠቀሱት ትክል ድንጋዮች መካከል ከስድስት ሺ በላይ የሚሆነው ትክል ድንጋይ በጌዲዮ ዞን ብቻ ይገኛል ብለዋል።



የጌዲዮ ዞን መልከአ ምድር አቀማመጥ

ያሉ ቅርሶችን ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለማስተዋወቅ «አካባቢን ማወቅ ሀገር ከማወቅ ይቀድማል» በሚል መሪ ቃል በማህበራትና በግል የተደራጁ የህብረተሰብ የሀገርህን እወቅ ክበባት የተለያዩ የማስተዋወቂያ አማራጮችን በመጠቀም በተሠራው ሥራ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ዞኑን እንዲጎበኙ ተደርጓል ብለዋል።

እንደ አቶ ዳንኤል ማብራሪያ፤ ከሰሞኑ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት የሳይንስና እና የባህል ድርጅት / ዩኔስኮ/ በዓለም ቅርስነት የተመዘገበው የጌዲዮ መልክአ ምድር በፌዴራል ቅርስና ጥበቃ ባለሥልጣንና የክልሉ ባህልና ቱሪዝ ቢሮ በጋራ በመሆን ጥናት ላይ በመመሥረት ባከናወኑት ሥራ የተገኘ ውጤት ነው። በኢትዮጵያ 10ኛ ሆኖ የተመዘገበው መልክአ ምድር በዞኑ ያሉ ሌሎች የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ መስህቦች በቱሪስቶች እንዲጎበኙ ትልቅ በር የሚከፍት ነው፡፡

በጌዲዮ ዞን የባህላዊ አስተዳደር ሥርዓት፣ የዳኝነት ሥርዓት፣ ባህላዊ የግጭት አፈታትና የደራሮ በዓልን በዩኔስኮ ለማስመዝገብ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ስለመሆኑም አቶ ዳንኤል ገልጸዋል።

ዜና



## “በመስከረም ወር ኢትዮጵያ እንግዳ ለመቀበል መዘጋጀቷን ማስተዋወቅ ያስፈልጋል”

- ጋዜጠኛ ሄኖክ ስዩም (ሀገሬ)

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በመስከረም ወር ያሉ በዓላትን ተከትሎ ኢትዮጵያ እንግዳ ለመቀበል መዘጋጀቷን ለውጭ ሀገራት ጎብኚዎች ማስተዋወቅ ያስፈልጋል ሲል የባህልና ቱሪዝም ጋዜጠኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ጋዜጠኛ ሄኖክ ስዩም (ሀገሬ) ገለፀ። ጋዜጠኛው መንግሥት በዓላት በሚከበሩባቸው አካባቢዎች ላይ ሰላምን የማስከበርና መሠረተ ልማትን የማሟላት ተግባርን መከወን እንደሚገባውም አሳስቧል።

ጋዜጠኛ ሄኖክ ስዩም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገረው፤ ክረምት ተፋዞ የሚከርመው የቱሪዝም ዘርፍ በመስከረም ወር ላይ ባሉ በዓላት የሚነቃቃበት ሁኔታ አለ፤ በመሆኑም ወሩን ተከትሎ ባሉ ባህላዊና ሃይማኖታዊ በዓላትን በሚመለከት ኢትዮጵያ እንግዳ ለመቀበል መዘጋጀቷን ለውጭ ሀገራት ጎብኚዎች ማስተዋወቅ ያስፈልጋል።

እንደ ጋዜጠኛው ገለጻ፤ በመስከረም ወር የሚገኙ በዓላት የሚገባቸውን ያህል ተዋውቀው ለዓለም ገበያ መሸጥ አልቻሉም። መስከረም ወሩን በሙሉ ለዓለም ገበያ መሸጥ የሚችል በርካታ ኩነት ያለበት ወር በመሆኑ ያለውን የበዓል ድባብ ዓለምአቀፍ የማስተዋወቅ ሥራ በመሥራት የውጭ ሀገራት የቱሪስት መዳረሻነቱን ማስፋት ያስፈልጋል።

መስከረም አንድ ተራ ወር ብቻ ሳይሆን በቱሪዝም ላይ ትልቅ አቅምና ልዩነት መፍጠር የሚችል ለዘርፉም መነቃቃትን መፍጠር የሚቻልበት ስለመሆኑ ጋዜጠኛ ሄኖክ ጠቅሷል።

የመስከረም ወር በዓላት ከፉክክር ወደ ትብብር የሚያድጉ መሆን አለባቸው ያለው ጋዜጠኛ ሄኖክ፤ አብዛኞቹ በተከታታይ ጊዜያት የሚከበሩ በዓላት መሆናቸውን ተከትሎ ተባብሮ የውጭ ሀገራት ጎብኚን ማብዛትና ማስተዋወቅ ያስፈልጋል ብሏል።

በወሩ ኢትዮጵያ ባለ 13 ወር ፀጋነቷን የሚመሰክረውን የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት ጨምሮ ግሸን ደብረከርቤ በዓል፣ ኢሬቻ፣ ጊፋታና ያሆዴ የሚከበሩበት ወር በመሆኑ በርካታ የውጭ ሀገራት ቱሪስቶችን ማግኘት የምትችልባቸው በዓላት ይገኛሉ።

የውጭ ሀገራት ጎብኚን ለመጨመር በሚደረገው እንቅስቃሴ በዓላቱን በተመለከተ የሚቀሩ የቤት ሥራዎች ስለመኖራቸው የጠቆመው ጋዜጠኛ ሄኖክ፤ በግሸን የሚከበረው በዓልም ኢየሱስ ክርስቶስ ከተሰቀለበት መስቀል ጋር ግንኙነት ካለው ስፍራ ላይ ማክበር የሚፈጥረውን የተለየ ድባብ በማስተዋወቅ የቱሪስት መዳረሻን ማስፋት እንደሚቻል ጠቁሟል።

የኢትዮጵያ ዘመን መለወጫ በሚያስፈልገው ልክ አልተዋወቀም ያለው ጋዜጠኛ ሄኖክ፤ መስቀል በዓልንም በሚመለከት የአንድ ቀን በዓል ብቻ አድርጎ ማሰብ አያስፈልግም ብሏል፤ የጉራጌ የመስቀል አከባበር ለቀናት የሚቆይና ዘርፈ ብዙ ጎኖቹን አስተዋውቆ ለዓለም ገበያ ማቅረብ ያስፈልጋል ሲልም አክሏል።

ጋዜጠኛ ሄኖክ ስዩም (ሀገሬ) መንግሥት በዓላት በሚከበሩባቸው አካባቢዎች ላይ ሰላምን የማስከበርና መሠረተ ልማትን የማሟላት ተግባርን መከወን እንደሚገባውም አሳስቧል።

# ያሆዴ የሰብዓዊነት፣ የፍቅር፣ የሰላም፣ የአንድነትና የይቅርታ በዓል ነው

**ታደሰ ብናልፈው**



ሀድያ፡- ያሆዴ የሀድያ ብሔር የዘመን መለወጫ የሰብዓዊነት፣ የፍቅር፣ የሰላም፣ የአንድነትና የይቅርታ በዓል ነው ሲሉ የሀድያ ዞን ዋና አስተዳደር አቶ አብረሃም መጫ ገልጸዋል።

አቶ አብረሃም መስከረም 11 የሚከበረውን የያሆዴን የሀድያ ብሔር የ2016 ዓመት የዘመን መለወጫ በዓል ዋዜማ አከባበር አስመልክተው ባደረጉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት፤ የያሆዴ በዓል የሰብዓዊነትና የመደጋገፍ ጥግ የሚታይበትና ፍቅር፣ አንድነት፣ ሰላም፣ ይቅርታና አብሮነት የሚገለጽበት የሀድያ ብሔረሰብ ባህላዊ በዓል ነው ብለዋል።

የያሆዴ በዓል ዘመድ አዝማድ የሚገናኝበት፣ የተጣላ የሚታረቅበት፣ ቂምና በቀል የያዘ ቂሙን ረስቶ አዲሱን ዓመት በፍቅር፣ በተስፋና በብልፅግና የሚቀበልበት ትልቅ በዓል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ያሆዴ የዘመን መለወጫ በዓል የሀድያ ብሔረሰብ የባለፈው ዓመት የደረሰበትን ችግር በጥንካሬ አልፎ በአዲስ ህልም ብርሃን የሚያይበት ነው ብለዋል።

ዓለም በተለያየ ዘመናት የተለያዩ አሉታዊና አወታዊ ክስተቶችን ስታልፍ ብዙ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ባህላቸውን፣ ቋንቋቸውንና እሴቶቻቸውን ከማጣት ባለፈ ከነጭራሹም ጠፍተዋል። የሀዲያ ማህበረሰብ ግን ባህሉን፣ እምነቱን፣ ቋንቋውን ጠብቆ ለትውልድ አስተላልፏል። ማህበረሰቡ ካሉት ብዙ ባህሎችም አንዱና ትልቁ ያሆዴ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

የሀድያ ማህበረሰብ የራሱ የመተዳደሪያ የሕግ ሥርዓት ቀርጾ የኖረ፣ የእርቅና የሥልጣኔ ታሪክ ያለው ትልቅ ብሔር ነው። ከአጎራባች ብሔሮችና ከመላ የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በአንድነትና በፍቅር የሚኖር ህዝብ ነው ብለዋል።

ማህበረሰቡ ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር በፍቅር፣ በሰላምና በአንድነት የመኖር እሴቱን አጠናክሮ ያስቀጥላል ሲሉም ገልፀዋል።

የያሆዴ የዘመን መለወጫ በዓልና ሌሎች ባህሎች ከዘመናት ዘመናት በምራዕባውያን ባህል ሳይመረዙ ተጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ ተሸጋግረዋል። ባህሎችን ለትውልዱ የማስተዋወቅና የማስተላለፍ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ጠቁመዋል።

የሀድያ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ሃላፊ አቶ ታምሬ ኤርሚያስ በበኩላቸው፤ ያሆዴ የሀድያ ብሔር ዘመን መለወጫ በዓል ከመሆን ባለፈ ወንድማማችነትን፣ አብሮነትንና ሰላምን የሚያፀናና የሚሰብክ የእርቅ በዓል ነው ብለዋል።

ያሆዴ የዘመን መለወጫ በዓል የተቸገሩ ወገኖች የሚጠየቁበት፣ የተራራቁ ዘመዶች የሚጠያየቁበት፣ የአንድነትና የአብሮነት ባህል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የያሆዴ የዘመን መለወጫ በዓል ባህላዊ እሴቱ ሳይሸራረፍ ለትውልድ እንዲተላለፍ የቀደሙ አባቶች ትልቅ ሥራ ሠርተዋል። ይህ የእርቅ፣ የሰላም፣ የመጠያየቅ፣ የአብሮነት በዓል ለትውልድ እንዲተላለፍ ቢሮው በትኩረት እየሠራ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል።

የሀገር ሽማግሌዎች በዓሉን ሲያከብሩ የተጣላን አስታርቀው በመሆኑ ብሔረሰቦች በሰላምና በፍቅር እንዲኖሩ እያደረገ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

በዓሉ በዓለም የቅርስ፣ የምርምርና ጥናት፣ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ በዩኒስኮ እንዲመዘገብ ተመራማሪዎች መሥራት አለባቸው ሲሉም አመላክተዋል።

# አውደ-ርዕዩ በዘርፉ የካበተ ልምድ ካላቸው ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በትብብር ለመሥራት እድል ፈጥሯል

## - የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር

በጋዜጣው ሪፖርተር




አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ለአንድ ወር የተካሄደው የውሃና ኢነርጂ አውደ-ርዕይ በዘርፉ ያካበተ ልምድ ካላቸው ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በትብብር ለመሥራት እድል መፍጠሩን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ገለጸ።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር "የውሃ ሀብታችን ለብልጽግናችን" በሚል መሪ ሃሳብ በሳይንስ ሙዚየም ለአንድ ወር ያካሄደው አውደ ርዕይ ተጠናቋል።

በሚኒስቴሩ የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ ጌትነት ጌጡ፤ በአውደ-ርዕዩ ዘርፉን ለማዘመን በትግበራ ላይ ያሉ የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ለዕይታ ቀርበዋል ብለዋል።

ለአብነትም ኢትዮጵያ የውሃ መጠኗን በዲጂታል መተግበሪያ በመታገዝ እንዴት እንደምትከታተልና እንደምትቆጣጠር ማሳየት መቻሏን ጠቁመዋል።

አውደ-ርዕዩን የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጨምሮ የዘርፉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ተወካዮች እንዲሁም አምባሳደሮች መጎብኘታቸውን ነው ያረጋገጡት።

በመሆኑም አውደ-ርዕዩ ሀገሪቱ በዘርፉ የምታከናውነውን ሥራ ለማስገንዘብ እድል ሰጥቷል ነው ያሉት።

ከዚህ በተጨማሪም አውደ-ርዕዩ በዘርፉ ከተለያዩ ተቋማት ጋር አዳዲስ አጋርነትና ትብብር ለመመሥረት ምቹ ሁኔታ መፍጠሩንም ገልጸዋል።

በመድረኩ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ያቀረቡ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በበኩላቸው አውደ-ርዕዩ የውሃና ኢነርጂ ዘርፍን በቴክኖሎጂ ለማዘመን የሠሯቸውን ሥራዎች ለሕዝብ ለማቅረብ እድል ሰጥቶናል ብለዋል።

በኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት በመረጃና ክላይማቶሎጂ ክፍል ተመራማሪ የሆኑት ለታ በቀለ ተቋማቸው በአውደ-ርዕዩ በሀገሪቱ ያለውን የአየር ፀባይ ሁኔታ ጥናት ለማካሄድ የሚጠቀምባቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶች ማቅረባቸውን ጠቅሰዋል።

የተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች አውደ-ርዕዩን መጎብኘታቸው ገልጸው ይህም በቀጣይ በሚቲዎሮሎጂ ዘርፍ አብረው መሥራት የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች ለመለየት ዕድል መፍጠሩን ነው የገለጹት።

የአነጋ ኢነርጃይዝ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ የሽያጭ ባለሙያ እየሩሳሌም ደጀኔ በበኩሏ በአውደ-ርዕዩ ኅብረተሰቡ የሚጠቀምባቸውን ኃይል ቆጣቢ ምድጃዎች ማቅረባቸውን ተናግራለች።

በዝግጅቱ ላይ መሳተፋቸው ኃይል ቆጣቢ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በቀላሉ ለማስተዋወቅ እንደረዳቸው በመግለፅ እንደ ሀገር መሰል አውደ-ርዕዮች በተለያዩ አካባቢዎች ሊስፋፉ እንደሚገባ ተናግራለች።

በሐፍ አስመጪና አቅራቢ ድርጅት የኦፕሬሽን ማናጀር ሃበን ገብሩ በአውደ-ርዕዩ ምንም አይነት ኤሌክትሪክ ኃይልና የውሃ ማጣሪያ ኬሚካል ሳይጠቀም ውሃን ማጣራት የሚችል ቴክኖሎጂ ለኅብረተሰቡ በስፋት አሳይተናል ብለዋል ሲል የዘገበው ኢዜአ ነው።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# «የብሪክስ አባልነት ተጨማሪ ወዳጆችን በተለየ መልክ የማፍራት ዕድል ያስገኛል»

- አምባሳደር ዲና ሙፍቲ
በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
የውጭ ግንኙነት እና የደህንነት ቋሚ ኮሚቴ አባል

ምሕረት ሞገስ

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ዳይሬክተር ጀኔራል ሆነው ሠርተዋል- አምባሳደር ዲና ሙፍቲ። በዚሁ ተቋም በተለያዩ ጊዜያት ሁለቴ በቃል አቀባይነት አገልግለዋል። በአሜሪካ እና በካናዳ ኤምባሲዎች አማካሪ ሆነው ሠርተዋል። በስዊድን የኢትዮጵያ ልዩ መልዕክተኛም ነበሩ። በዙምባቡዌ፣ በኬንያ እና በግብፅ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች አምባሳደር ሆነው ሠርተዋል። አሁን ደግሞ የውጭ ግንኙነት እና የደህንነት ቋሚ ኮሚቴ አባል ሆነው በመሥራት ላይ ይገኛሉ።

እኚህ በዲፕሎማሲው መስክ በስፋት የሠሩት አምባሳደር ዲና፤ ያስፈው ዓመት የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴን እንዴት አዩት? የሀገሪቷን የዲፕሎማሲ ዘርፍ ተግዳሮት እና ስኬቷን በተመለከተ ምን ይላሉ? ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል ከመሆኗ ጋር ተያይዞ የሚገኘው ጥቅም እና የሚያስከትለው ስጋት እንዲሁም ስለወደፊቱ የዲፕሎማሲ መንገድ በማንሳት ቆይታ አድርገን እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል። መልካም ንባብ፡-

**አዲስ ዘመን፡- ያስፈው ዓመት የሀገሪቱ የዲሎማሲ ጉዞ ምን ይመስላል ከሚለው ብንጀምርስ?**

**አምባሳደር ዲና፡-** ባሳለፍነው አሮጌ ዓመት በዲፕሎማሲው መስክ በርካታ ተግዳሮቶች የመኖራቸውን ያህል በጥሩ መልኩ ሊጠቀሱ የሚችሉ ትልልቅ ውጤቶችም ነበሩ። ተግዳሮቶቹ የሚታወቁ ናቸው። ዋነኛው በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል የነበረውን ጦርነት ተከትሎ የነበረው ዲፕሎማሲያዊ ሁኔታ ነው። ነገር ግን ያም ቢሆን በሰላማዊ መንገድ የተደረጉት እንቅስቃሴዎች ውጣ ውረዶች ቢኖራቸውም መጨረሻ ላይ ችግሩን በመፍታት፣ ስምምነት ላይ መደረሱ አንድ ትልቅ ውጤት ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል። እዚህ ላይ ተጠቃሽ ሊሆን የሚችለው የፕሪቶሪያው ስምምነት ነው። ይህ እንደ አንድ የዲፕሎማሲ ውጤት ሊወሰድ ይቻላል። ምክንያቱም ሁልጊዜም ተግዳሮቶች በሌላ በኩል ዕድሎችን ይዘው የሚመጡ ሲሆን፤ በዚህም መንገድ የሠላም ዕድል ተገኝቷል።

ሌላው በዚህ ዓመት በተጠቀሰው ጦርነት ምክንያት ከተለያዩ አቅጣጫዎች እና ከተለያዩ ወገኖች በርካታ ጫናዎች ነበሩ። እነዚህን ጫናዎች ለመቋቋም የተደረጉ ጥረቶች ከሞላ ጎደል ስኬታማ ናቸው። ይኸው ጫናም እያለ ከሞላ ጎደል ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ተመዝግቧል።

ባሳለፍነው ዓመት ሌላው እንደትልቅ ውጤት የሚታየው የኢትዮጵያ የብሪክስ አባልነት ነው። አንደኛ የኢትዮጵያ የብሪክስ አባልነት የዲፕሎማሲውን ምህዳር ያሰፋል፤ ከነበሩት ወዳጆች ጋር ያለው ግንኙነት እንዳለ ሆኖ፤ ተጨማሪ ወዳጆችን በተለየ መልክ የማፍራት ዕድል ያስገኛል። ይህ ንግድን በማሳለጥ፣ ኢንቨስትመንትን በመጨመር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማፋጠን እና በአጠቃላይ የዲፕሎማሲና የፖለቲካ መደጋገፍን በመፍጠር ረገድ የሚያመጣው ውጤት ትልቅ ነው። ስለዚህ የብሪክስ አባልነት እንደአንድ ትልቅ ግኝት ሊጠቀስ የሚችል ነው።

በተጨማሪ ኢትዮጵያ በተለያዩ መድረኮች ስትሳተፍ ቆይታለች። አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ መድረኮች ላይ ነበረች። እነዚህ መድረኮች ላይ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስጠብቁ አቋሞች የተራመዱባቸው እና ተፈላጊ ውጤቶችም የተገኙባቸው መድረኮች ናቸው። ይህ እንግዲህ ኮቪድ፣ ጎርፍ እና አልፎ አልፎ ድርቅ እንዲሁም ከሰሜኑ አካባቢ በተጨማሪ በሌሎች አካባቢዎችም ግጭቶች እያለ የተደረጉ መሆናቸው መረሳት የለበትም።

በአጠቃላይ ባሳለፍነው ዓመት የሀገራችን የዲፕሎማሲ ቁመና ሀገራችንን ከተግዳሮት፣ ከጫና ለማላቀቅ የተደረጉ ጥረቶች ውጤታማ ሆነው የታዩ ናቸው ማለት ይቻላል። በተገኙት ጥሩ ጥሩ ውጤቶች ላይ ተመስርቶ ወደ ፊት በስፋት መሥራት አለበት።

> ብሪክስ አምስት ሀገራትን በጨመረ በጥቂት ቀናት ውስጥ (የጂ 20) ቡድን ሃያም አፍሪካን እንደአንድ አባል አድርጎ ወስዷል። እዚህ እና እዚያ አንዱ ሌላውን የመመልመል እና የመሳብ ነገር ይታያል



**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ ኢትዮጵያ የምትከተለው የዲፕሎማሲ ፖሊሲ አካታች ነው ይባላል። ምን ማለት ነው?**

**አምባሳደር ዲና፡-** አካታች ዲፕሎማሲ የምንለው የሀገራችንን ጥቅም እስካራመደ ድረስ፤ የሀገር ጥቅም ሲባል ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሌሎችም የኢንቨስትመንት፣ የቱሪዝም ...ወዘተ ጥቅሞች፤ እያልን ልንዘረዝር የምንችለውን ጥቅም ለኢትዮጵያ እስካስገኘ ድረስ ከየትኛውም ሀገር ጋር መገናኘት እና አብሮ መሥራትን የሚመለከት ነው ።

የትኛውም ሀገር በሚያራምደው ርዕዮተ ዓለም ምክንያት፣ በድንበር፣ በቦታ ርቀት ወይም በአቀማመጡ እና በሚከተለው የተለየ መንገድ ምክንያት ኢትዮጵያ አታገልለውም፤ ችግር ቢኖርበትም ኢትዮጵያ ከዚያ ሀገር የምትፈልገው የለም ማለት አይደለም፤ ከዚያ ሀገር የምትፈልገው እና ያ ሀገር የሚጠቅማት ከሆነ ከእዚያ ሀገር ጋር ትገናኛለች ማለት ነው። እዚህ ላይ ግን ዞሮ ዞሮ ሰጥቶ በመቀበል መርህ፤ ሁሉን ባካተተ መልኩ፤ የሌሎቹንም ሆነ የእኛን ሀገር ጥቅም ግምት ውስጥ በማስገባት፤ ያንንም በማራመድ ላይ መመስረት ማለት ነው።

በዚህ በመሠረታዊ የውጭ ግንኙነት መርሆች የሚካሔድ፤ ሁሉንም ወገኖች ማለትም በየትኛውም ማዕዘን ያሉ የዓለም ሀገሮች እና በየትኛውም አካባቢ ያሉ ተቋማት፤ አህጉራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶችን ያካተተ አካሔድ አካታች የዲፕሎማሲ መንገድ ነው ማለት ይቻላል። አካታች ዲፕሎማሲ በቀላሉ የኢትዮጵያን ጥቅም መሠረት አድርጎ ከሁሉም ጋር መደራደር እና መገናኘት ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁናዊ የዓለም የኃይል አሰላለፍን በተመለከተ ምን ይላሉ?**

**አምባሳደር ዲና፡-** ዓለማችን የተለያዩ የኃይል አሰላለፎችን ያስተዋለችባቸው የተለያዩ ዘመኖች አሉ። አንድ ዘመን አንድ ብቸኛ ሀገር ልዕለ ኃያል ሆና የቆየችበት ዘመን ነበር። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የሁለት ዋልታ ሥርዓት (ባይ ፖላር ሲስተም) የተሰኘ ሁለት ልዕለ ኃያላን የነበሩበት ዘመን ነበር። በአንድ በኩል ወደ ብዙ ሀገሮች የተከፋፈለችው ሶቪየት ኅብረት የተባለች ሀገር እና በሌላ በኩል አሜሪካ በአንድ በኩል ሆነው ነበር። እነዚህ ሁለት ዋልታዎች ናቸው፤ እዚህ ላይ ሁለት ኃያላን ነበሩ። በዚያ ጊዜ የአንዱ ዋልታ ላይ መሆን ግድ ነበር። ከሁለቱም ገለል ለማለት የሞከሩም ነበሩ። ያም ብዙ የሚያዋጣ አልነበረም፤ ለማንኛውም ግን ሁለት ዋልታ ነበር፤ ይህ አልፏል።

ቀጥሎ የብዙ ዋልታዎች ሥርዓት (መልቲ ፖላር ሲስተም) ዓለም አለ። ይህ አሁን ያለው ዓለም ማለት ነው። አሁን ላይ ሁለት ብቻ ሳይሆን ሌሎች ኃያል ነን የሚሉ የመጡበት ዘመን ነው። እዚህ ላይ የተለያዩ ሀገራት ኢኮኖሚያዊ ጡንቻቸውን ያዳበሩበት፤ በኢኮኖሚ አቅማቸውም የጠነከሩበት ተፅዕኖ ማሳረፍ የሚችሉበት ሁኔታ የተፈጠረ በመሆኑ፤ አሁን ዓለማችን የብዙ ዋልታዎች ዓለም ናት ማለት ይቻላል። ባለአንድ ዋልታ አልፏል፤ ሁለት ዋልታም የለም። አሁን እዚህም እዚያም የተለያዩ ኃያሎች አሉ። ተፅዕኗቸውም በሁሉም በኩል የተለያየ ነው። ለምሳሌ ቀይ ባህር አካባቢ ራሳቸውን እንደኃያል ሀገር የወሰዱና ቀይ ባህር አካባቢ የፖለቲካውንም ሆነ የደህንነቱን ሁኔታ ለመቆጣጠር የሚሞክሩ አሉ።

በሌላ በኩል የሚሻኮቱ አሉ፤ በተለይ ወታደራዊ መሠረት ለመጣል ሽኩቻዎች መኖራቸው የሚካድ አይደለም። ከፍተኛ የጦር መሣሪያ ዝውውርም አለ። አሁን ባለው ሁኔታ ግን ውድድሮች እና ሽኩቻዎች፤ እዚህ እና እዚያ መገፋፋቶች የበዙበት ጊዜ ነው። ስለዚህ አሁን ዓለም ብዙ ዋልታዎች ያሉባት ሲሆን፤ ይህ አሁን ላይ እየሠከነ ሳይሆን ብዙ ሂደትን ተከትሎ እየዘለቀ ነው። ልዕለ ኃያል የሚሆነው ማን ነው? የሚለው ገና ወደ ፊት የሚታወቅ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- የብሪክስ መፈጠር የዓለምን የኃይል አሰላለፍ አይቀይረውም?**

**አምባሳደር ዲና፡-** ብሪክስ በፊትም ነበር። ብሪክስ ውስጥ ያሉት አምስት አባል ሀገራት ማለትም ቻይናን እና ራሺያን የመሳሰሉ ልዕለ ኃያል ሀገሮች አሉ። ከእኛ ክፍለ አህጉር ደቡብ አፍሪካ አለች። ከላቲን አሜሪካ ብራዚል እና ከኤዢያም ሕንድ አለች። አሁን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አምስት ሀገራት ተጨምረዋል። ወደ ፊት ሌሎችም የሚጨመሩ ይሆናል። አሁን ብሪክስ አምስት ሀገራትን በጨመረ በጥቂት ቀናት ውስጥ (የጂ 20) ቡድን ሃያም አፍሪካን እንደአንድ አባል አድርጎ ወስዷል። እዚህ እና እዚያ አንዱ ሌላውን የመመልመል እና የመሳብ ነገር ይታያል።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃስ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## «የብሪክስ አባልነት...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

በእርግጥ እነዚህ የብሪክስ ሀገራት መካከል ልዩነት የለም ማለት ባይቻልም እርስ በእርስ ይነግዳሉ። ለምሳሌ ቻይና ከአሜሪካን ጋር ትነግዳለች። የድሮ ቻይና አይደለችም። ሩሲያም ከዩክሬን ጋር ጦርነት ውስጥ በመግባቷ የተነሳ የተለየ ጦርነት የተፈጠረ ቢሆንም፤ እርስ በእርስ መገናኘትም አለ፤ መገፋፋትም እንዲሁ እየታየ ነው። ስለዚህ የዓለም የኃይል አሰላለፍ እዚህ ጋር ነው። የበላይ ሆኖ ዓለምን የሚያሽከረክረው ይኸኛው ነው፤ ለማለት ይከብዳል። ሁሉም የራሱ ሚና አለው። በብሪክስም ተመሳሳይ ነው።

ብሪክስ እየተጠናከረ የመሔድ ዕድሉ በጣም ሰፊ ነው። አሁን ብሪክስ ብዙ ሀገራትን እየተቀበለ ነው። ሳዑዲን ግብፅን እና ኢትዮጵያን ጨምሮ አምስት ሀገሮችን አካቷል። አባላት በጨመረ ቁጥር ሀብት ይጨምራል፤ ሀብት በጨመረ ቁጥር ቴክኖሎጂ ይጨምራል። ቴክኖሎጂ በጨመረ ቁጥር ወታደራዊ ኃይሉም ብቃቱም ይጨምራል። ዞሮ ዞሮ የዓለም የበላይነት ያልለየለት የመገፋፋት ነገር እንዳለ መረሳት የለበትም። ነገር ግን እኛ ከእዚህ የኃይል አሰላለፍ መጠቀም አለብን። ከሁሉም ጋር እንደየጥቅማችን እና ፍላጎታችን፤ የሚደርሰንን ነገር የማግኘት እና ግንኙነታችንን የማሳደግ ዕድል አለን።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ የብሪክስ ቡድን አባል መሆን በሌሎች ዘንድ እንደመልካም ሳይታይ ይችላል። እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አምባሳደር ዲና፡-** ትክክል ነው። ብሪክስ ውስጥ ያሉ ሀገራት ይታወቃሉ። በተለይ አንዱ የብሪክስ ሀገር ጦርነት ውስጥ መግባቱን ተከትሎ ጦርነት ውስጥ የገባው ሀገር፤ ከአንዳንድ ምዕራባውያን ጋር ትልቅ ቅራኔ ውስጥ ገብቷል። ስለዚህ ከብሪክስ ጋር መቀላቀል ከእዚያ ሀገር ጋር ቅራኔ ውስጥ ከገቡ ሀገራት ጋር የተለየ ስሜት ይፈጥራል። እከሌ የተባለ ሀገር ለምን ብሪክስን ተቀላቀለ? የሚል ምስቅልቅል ያጋጥማል፤ ሆኖም ምንም ማድረግ አይቻልም።

ኢትዮጵያ ብሪክስ ውስጥ የምትገባው ከእነርሱ ጋር ለመሚገት እና ለመጣላት ሳይሆን የራሷን ጥቅም ለማስከበር እስከሆነ ድረስ የእነርሱን ጥቅም ለመንካት አይደለም የሚለው በደንብ መወሰድ አለበት። ነገር ግን እነዚህ ቅሬታዎች የማይቀሩ መሆናቸውን ለመካድ አይቻልም። ሃሜቶች እና ግምቶች ይኖራሉ። ለምሳሌ ኢትዮጵያ ብሪክስ የገባችው እንዲህ ስለሆነ ነው ሊባል ይችላል። ይህ ብዙም አይጠቅምም። ዋናው የሚጠቅመው እውነታውን ማየት ነው።

ሁልጊዜም ተራማጅ የሆነ ሊተገበር እና ውጤታማ መሆን የሚችል የውጭ ግንኙነት ያስፈልጋል። ይህ መንገድ እጅግ ጠቃሚ ነው። ምንጊዜም ጂኦግራፊ እና የሚከተሉት የፖለቲካ ሥርዓት መስፈርት አይሆንም። መስፈርቱ ከብሔራዊ ጥቅም አኳያ መታየት አለበት። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ምንጊዜም ጠቃሚ እና ወደፊትም ውጤታማ የሚያደርግ ነው።

**አዲስ ዘመን፡-በብሪክስ ሀገሮች መካከል ያለው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ግንኙነት ብሪክስ ላይ የሚፈጥረው ተፅዕኖ ምን ያህል ነው? እዚህ ላይ ለምሳሌ በሕንድ እና በቻይና መካከል ያለውን የድንበር ውዝግብ መጥቀስ ይቻላል። እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አምባሳደር ዲና፡-** ከላይ እንደገለፅኩት ነው። በሀገሮች መካከል ፍፁም የሆነ ግንኙነት የለም። በተለይ ጉርብትና ያላቸው ሀገሮች ግንኙነታቸው ትንሽ ከፍተት ሊኖረው ይችላል። አንዱ ሌላውን የሚጠረጥርበት፣ አንዱ ሌላውን የሚገፋበት፣ በሀብት ምክንያት፣ በድንበር እና በሉዓላዊነት ምክንያት የተለያዩ መሻከሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ይሔ በጥያቄው እንደተነሳው በፊትም የነበረ እና ያለ ነው። ይህ እያለም ቢሆን የሀገሮቹን ሁኔታ እነርሱ የሚገልፁበትን መንገድ እነርሱ ሊገልፁት ይችላሉ። ነገር ግን የብሪክስ ሀገሮችም የሚያዩት በዋናነት የሀገራቸውን ጥቅም ነው። በመካከላቸው ያለው ነገር እንዳለ ሆኖ ትልቁን ስዕል አይተው የተሰበሰቡ በመሆኑ የብሪክስን ጠቀሜታ ይዘው ይቀጥላሉ ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ብሪክስ ግን የአንዳንድ ምዕራባውያንን ጫና ከመቋቋም አንጻር ስኬታማነቱ ምን ያህል አስተማማኝ ይሆናል ብለው ይገምታሉ?**

**አምባሳደር ዲና፡-** ስኬታማነቱ አባል ሀገራቱን የሚመስል ነው። አባል ሀገራቱ ደግሞ እነማን እንደሆኑ ይታወቃል። አሁን ቅድም በተባሉት ሀገራት መካከል ልዩነቱ አለ። ጫናው ሊኖር እና ሊቀጥል ይችላል። ጫናው ግን ይታወቃል። በዓለም አንዱ አንዱን የመገፋት፤ አንዱ ሌላውን የመጥቀም፤ አንዱ አንዱን የማቅረብ እና አንዱ ሌላውን የማራቅ አለ። ይህ እንዲሁ እንዳለ ይቀጥላል ማለት ነው። ጫና ይኖራል፤ ጫናው አንፃራዊ በሆነ መልኩ ውጤቱ የሚታይ ነው። ብሪክስ ነበር፤ አሁንም አለ። ወደ ፊትም ይቀጥላል። አሁን ደግሞ ሀገራትን እየጨመረ በመሆኑ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሆኖ እየዳበረ የሚሔድ ዕድሉ በጣም ሰፊ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- የብሪክስ መፈጠር ስታዳጊ ሀገራት ምን ያህል ይጠቅማል?**

**አምባሳደር ዲና፡-** ታዳጊ ሀገራት ሀብታቸውን በአግባቡ ለመጠቀም ያግዛቸዋል። አግባብ ያለው ንግድ መሳብ ይችላሉ። ምክንያቱም አባል ሀገሮቹ ትልልቅ ናቸው። የእነርሱንም ኢንቨስትመንት የመሳብ ዕድል ያገኛሉ። በቱሪዝም መስክም ብዙ ቱሪስቶች ከእነዚህ ሀገሮች የሚመጡበት ሁኔታ ይኖራል። በቴክኖሎጂ በኩልም የአንዱን ቴክኖሎጂ አንዱ የመሳብ ዕድል ይኖረዋል። ይህ በአጠቃላይ ለመጠቃቀም የሚመች ሲሆን፤ በተለይ ለታዳጊ ሀገሮች እጅግ ይጠቅማል።

**አዲስ ዘመን፡- እሺ ኢትዮጵያ አሁን አባል ሆነች። በዚህ ምክንያት አንዳንድ ምዕራባውያን ቅር ሲሰኙ እንደሚችሉ ይገመታል። ሀገሪቱ አባል ስትሆን የሚኖረው ጥቅም እና የሚያስከትለው ጉዳት ምን ያህል ተጠንቷል?**

**አምባሳደር ዲና፡-** ኢትዮጵያ የማን ወዳጅ መሆን እንዳለባት ለመወሰን የሌላ ሀገር ፍቃድ አያስፈልጋትም። ሉዓላዊ ሀገር ናት። ስለዚህ አሁንም ቢሆን የፈለገችው ማኅበር ውስጥ ተቀላቅላ አባል ለመሆን የምትወስነው ለራሷ ራሷ ኢትዮጵያ ናት። ኢትዮጵያ ስንል ሕዝቧ ማለት ነው። ሕዝቧ የመረጠው መንግሥት በፈለገው ማኅበር እና ድርጅት አባል መሆን ይችላል። ከላይ እንደገለፅኩት ነው። አሁን ባለው ዓለም ከዚህ ጋር ለምን ወዳጅ ሆንክ? የሚል ኃይል ብዙም ተቀባይነት የለውም። የብሪክስ አባል አሁን ብንሆንም ከአባል ሀገሮቹ ጋር በፊትም ወዳጆች ነን። ከቻይና ጋር በፊትም ሰፊ ወዳጅነት አለን። ትልቅ የኢኮኖሚ ግንኙነት አለን። ከሩሲያ ጋርም የቆየ ወዳጅነት አለን። ከሕንድ ጋርም ያለን ግንኙነት ይታወቃል። ስለዚህ ከእነርሱ ስብስብ ጋር መሆን ምንም ችግር የለውም። ምክንያቱም በግል ደረጃ ጠንካራ ወዳጅነት ካለን ተሰባስበው በማኅበራቸው ውስጥ መገኘቱ ምንም ችግር የለውም። በዚህ መልኩ ማየቱ የተሻለ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከአንዳንድ ምዕራባውያን ጋር ያለንን ግንኙነት ሊያሳሳው ይችላል የሚል ሃሳብ ይሰነዘራል። ምን ያህል ተጠንቷል ያልነው ለዚሁ ነው። እርስዎ ለዚህ ምላሽዎት ምንድን ነው?**

**አምባሳደር ዲና፡-** ከአንዱ ሀገር ጋር ወይም ከአንድ ተቋም እና ድርጅት ጋር የምንፈጥረው ግንኙነት በሌላው ኪሳራ ማካካስ የለብንም የሚል አቋም አለ። ግንኙነትም ሆነ አባልነት አንዱን በማክሰር ወይም አንዱን በመጫን እና ጥቅሙን በመጋፋት አይደለም። ዞሮ ዞሮ ጥቅም የጋራ ነው። እንዲህ ባለ ጉዳይ ላይ ሁሉም መጠቃቀም ይችላል። ጉዳዩ የጋራ ተጠቃሚነት ነው። የጋራ ተጠቃሚነትን ግምት ውስጥ ያስገባ ስለሆነ ሌሎችም በዚህ ደረጃ ገፍተው የሚቃወሙበት ምክንያት አይኖርም። እነርሱም ቢሆኑ ከእነዚህ ከብሪክስ አባል ሀገሮች ጋር ግንኙነት አላቸው። ሕንድ ከምዕራቡ ዓለም ጋር ጠንካራ ግንኙነት አላት። ብራዚል ከምዕራቡ ዓለም ጋር ጠንካራ ግንኙነት አላት። ታዲያ ኢትዮጵያ ጋር ሲደርስ ለምን የተለየ ይሆናል? ኢትዮጵያ ለምን ትቸገራለች? ለምን አባል ሆና አትጠቀምም?

**አዲስ ዘመን፡- ምዕራባውያን የተባበሩት መንግሥታትን የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ ሆኑ አህጉራዊ ድርጅቶችን በመጠቀም በሀገራት ላይ ጫና እንደሚያሳድሩ የሚታወቅ ነው። በብሪክስ በኩልስ ተመሳሳይ ጫና ሲፈጠር ስላለመቻሉ ምን ያህል እርግጠኛ መሆን ይቻላል?**

**አምባሳደር ዲና፡-** አሁን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ላይ ለውጥ ለማምጣት ትልቅ የሪፎርም ሥራ እየተሠራ ነው። ይህ ጉዳይ የብዙ ታዳጊ ሀገሮች አጀንዳ ነው። ምክንያቱም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በተለይም የፀጥታው ምክር ቤት ሪፎርም ያስፈልገዋል። እኛ ጋር የተወሰኑ አካባቢዎችን የወከሉ ሀገሮች አሉ።



**አራተኛው የሕዳሴ ግድብ ውሃ ሙሌት ትልቁ የዲፕሎማሲ ሥራ ስኬት ማሳያ ነው**

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ላይ አፍሪካ አባልነት ይገባታል፤ የላቲን አሜሪካ ሀገሮችም አባልነት መኖር አለበት የሚል የቆየ አጀንዳ አለ። በዚህ ረገድ በተባበሩት መንግሥታት በኩል የሚገፋው ነገር ብዙም ተቀባይነት አይኖርም። ደግነቱ እዚያም በተለይ በፀጥታው ምክር ቤት ውስጥ ድምፅን በድምፅ የመሻር ዕድል አለ። ኢትዮጵያ ደግሞ እዚያ ውስጥም ጠንካራ ወዳጅ ያላት በመሆኑ፤ ከዚህ ቀደምም እንደታየው በወዳጆቻችን አማካኝነት የተጠቀምንበት ሁኔታ አለ።

በዚህ በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ጥበቃ ምክር ቤት ውስጥ እኛ ላይ ሊጫን የነበረውን አንዳንድ አጀንዳዎች ድምፅን በድምፅ በመሻር የመጠቀም መብታቸውን ተጠቅመው ውድቅ ያደረጉበት ሁኔታ አለ። ስለዚህ አሁንም የሚታየው በዚህ ደረጃ ነው። ስለዚህ የብሪክስ አባል ሀገራት የምዕራባውያኑን ስህተት ይደግማሉ የሚል እምነት የለኝም።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በሕዳሴው ግድብ ላይ አራተኛ ሙሌት አከናውናለች በዲፕሎማሲው መስክ የሚኖረው ጠቀሜታ ምን ያህል ነው ?**

**አምባሳደር ዲና፡-** አራተኛው የሕዳሴ ግድብ ውሃ ሙሌት ትልቁ የዲፕሎማሲ ሥራ ስኬት ማሳያ ነው። ይህ በጣም ትልቅ ነገር ነው። ይህ በሀገር ደረጃ ኢትዮጵያውያን ከተባበርን ምን ያህል ውጤት ማምጣት እንደምንችል በደንብ ያሳየንበት ነው። ሁለተኛ በግድቡ ላይ እስከ አሁን የነበሩትን የዲፕሎማሲ መስክ ጫናዎችን ተቋቁመን እዚህ የደረሰንበት በመሆኑ፤ ትልቅ ሀገራዊ ስኬት ነው። ከዲፕሎማሲያችን አንፃርም ኢትዮጵያ ልትኮራበት የሚገባ ሲሆን፤ የሕዳሴ ግድቡ ሌሎች ሀገሮችን ለመበደል ሳይሆን ኢትዮጵያን እና አልፎ ተርፎ ሌሎችንም ይጠቅማል ተብሎ የተሠራ መሆኑን ማወቅ አለባቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ እጅግ አመሰግናለሁ።**

**አምባሳደር ዲና፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ኢትዮጵያና አልጀሪያ ግንኙነታቸውን ለማሳደግ በጋራ እየሠሩ ነው

## - ከአልጀርስ ወደ አዲስ አበባ ቀጥታ በረራ ተጀምሯል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያና አልጀሪያ የሁለትዮሽና የባለብዙ ወገን ግንኙነታቸውን ለማሳደግ በጋራ እየሠሩ መሆኑን በአልጄሪያ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር ነቢያት ጌታቸው አስታወቁ።

በአልጄሪያ የትራንስፖርት ሚኒስትር የሚመራ ልዑካን ቡድን በኢትዮጵያና በአልጄሪያ መካከል የመጀመሪያ የሆነውን ቀጥታ በረራ በትናንትናው ዕለት አስጀምሯል።

በማስጀመሪያ ሥነሥርዓቱ ላይ አምባሳደር ነቢያት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ እና የአልጀሪያ ሁለትዮሽ ግንኙነት ሲያተኩር የኖረው በፖለቲካና በዲፕሎማሲ መስክ ነው። የሀገራቱን የሁለትዮሽና የባለብዙ ወገን ግንኙነቶች ከአልጄሪያ ጋር በጋራ ሲሰራ ቆይቷል፤ አሁንም እየተሠራ ነው።

እንደ ረጅም ጊዜ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸው መጎልት የነበረበት፣ ያልዳበረውና ያላደገው ኢኮኖሚና የንግድ ልውውጡ ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ ይህን ለማሻሻል ቀጥታ የአየር በረራ በአልጀርስና በአዲስ አበባ መካከል መጀመር ወሳኝ የሆነ ትኩረት የተሰጠው ሥራ ነበር ሲሉ አብራርተዋል።

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያና አልጄሪያ ረጅም ዘመናት ያስቆጠረ የሁለትዮሽ ግንኙነት አላቸው። እ.ኤ.አ ከ1962 አልጄሪያ ነጻነቷን ከተቀዳጀችበት ጊዜ ጀምሮ ሁለቱ ሀገራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መሥርተው የሁለትዮሽ ግንኙነታቸውን በተሳካ ሁኔታ ሲያካሂዱ ቆይተዋል።



ከዓመት በፊት የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ሳሕለወርቅ ዘውዴና ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በአልጀሪያ ይፋዊ ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት ከአልጄሪያው ፕሬዚዳንት ጋር ባደረጉት ውይይት በሁለቱ ሀገራት መካከል የቀጥታ በረራ ማስጀመር፤ የንግድ ልውውጡንና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱን ማጎልበት የሚሉ በመሆናቸው ተከታታይ ሥራዎችን በመሥራት ከአልጀርስ ወደ አዲስ አበባ ኤር አልጀሪያ የመጀመሪያውን ቀጥታ በረራ አከናውኗል ብለዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተመሳሳይ ግንኙነት ለማድረግ የራሱን ዝግጅት የሚያካሂድ ይሆናል ያሉት አምባሳሩ፤ የቀጥታ በረራው ከታሪካዊነቱ ባሻገር የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ያሳድገዋል። በተለይ በንግድና ኢንቨስትመንት ትስስርና የህዝብ ለህዝብ ትስስሩን እንደሚያዳብረው አምባሳደር ነቢያት ገልጸዋል።

የአልጄሪያ የትራንስፖርት ሚኒስትር ዩሱፍ ሸረፋ በበኩላቸው፤ በአልጀርስና በአዲስ አበባ የመጀመሪያ ቀጥተኛ በረራ መጀመሩ ለሁለቱ ሀገራት ጠቃሚ ርምጃ መሆኑን ጠቁመው፤ የቆየውን ወዳጅነትና ትብብር ለማጠናከር ትልቅ ርምጃ መሆኑን ገልጸዋል። ቀደም ሲል በመሪዎች ደረጃ ከተገቡ ስምምነቶች መካከል አንዱ በመሆኑ በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን ታሪካዊ ግንኙነት የሚያጠናክር ነው ሲሉም አክለዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ባለፈው ዓመት በአልጄሪያ በሁለቱ ሀገራት መካከል በነበረ ውይይት ቀጥተኛ የአየር በረራ እንዲኖር ከስምምነት ተደርሶ ተግባራዊ መሆኑ በሁለትዮሽ ትብብር ላይ አዲስ ለውጥ ለማምጣት አስተዋፅኦ ያደርጋል። በተለይም ለኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ፣ ንግድን ለማፋጠን፣ የሰዎችን ዝውውርና የእቃዎች መጓጓዝ የተሳለጠ እንዲሆን ሚናው የጎላ ነው።

ሚኒስትሩ የኢትዮጵያ አየር መንገድም በአልጀርስ ቀጥተኛ የአየር በረራ እንዲጀምር ግብዣ አቅርበዋል።

# "ሀገር በቀል የኢኮኖሚ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ዶክተር እዮብ እንዳመለከቱት፤ የግሉን ዘርፍ ኢንቨስትመንት ከባቢ በማሻሻል በፈጠራ ላይ ኢንቨስት የማድረግ፣ በተለያዩ ዘርፎች አቅምን የመፍጠር፣ በምርምርና በልማት ላይ ኢንቨስት የማድረግ አቅሞች እንዲጠናከሩ ይደረጋል።

መንግሥት በሁለተኛው ሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ የሀገሪቱን ችግሮች ሊፈታ በሚችል መልኩ የግሉ ሴክተር ማድረግ ያልቻለውን ይሠራል ሲሉ አስረድተዋል።

የኢኮኖሚ ማሻሻያውን ውጤታማ ለማድረግ የሲቪል ሰርቪሱን አቅም ማሳደግ እንደሚያስፈልግ የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ኢኮኖሚውን መደገፍ የሚችል የሥራ ፈጠራና የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖር ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

በ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ የተቀመጡ ግዙፍ የልማት ግቦችን ለማሳካት ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ በመሆኑ ዓለም አቀፋዊና የሀገር ውስጥ ፈተናዎችን በመቋቋም በመጀመሪያው ሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ ተችሏል ብለዋል።

ዶክተር እዮብ እንዳስታወቁት፤ የሁለተኛው ምዕራፍ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ አራት ቁልፍ ምሰሶዎች አሉት።

በኢኮኖሚ ማሻሻያው የማክሮ ኢኮኖሚውን ማረጋጋት፣ የግሉ ዘርፍ ንግድና የኢንቨስትመንት ከባቢን ማሻሻል፣ የአየር ንብረትን በማሻሻል ምርታማነትን ማሳደግ እንዲሁም ብቃት ያለው የሲቪል ሰርቪስ መፍጠር ላይ ትኩረት ተደርጓል ብለዋል።

በንግዱ ዘርፍ የተሻለ ኢንቨስትመንት እንደሚጠበቅ ጠቁመው፤ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት እንዳለ ገልጸዋል።

በሀገሪቱ የንግዱን ዘርፍ ለማሻሻል የፈቃድ አሰጣጥና የግብር አሠራሮችን ዲጂታል ማድረግ፣ የመንግሥት አገልግሎቶች ደረጃቸውን የጠበቁና ዘመናዊ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

በኢንቨስትመንት ዘርፉ ለባለሀብቶች የንብረት ጥበቃ፣ የሕግ ከለላና መተማመንን የማጎልበት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ጠቅሰው፤ በኢትዮጵያ የንግድና የኢንቨስትመንት ሁኔታ ለመፍጠር ዝግጅት መደረጉን ገልጸዋል።

የግል ዘርፍ፣ የሥራ ፈጠራ፣ የክህሎት ትኩረት ወሳኝ የኢኮኖሚ ድርሻዎች በመሆናቸው፤ በኢኮኖሚ ማሻሻያ ማጠቃለያው ንቁና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የግል ዘርፍ ለመፍጠር እንደሚሠራ አስታውቀዋል።

የሁለተኛው ኢኮኖሚ ማሻሻያ በማዕድን፣ በሎጂስቲክስ፣ በቱሪዝም፣ በግብርና ምርታማነትና ተወዳዳሪነት ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ ጠቁመዋል።

የግሉ ዘርፍና የሥራ ፈጠራው ሲታሰብ የኢንዱስትሪ ዘርፉ የተሳሰረ ቁርኝት እንዳለው የተናገሩት ዶክተር እዮብ፤ ከኢንዱስትሪው ዘርፍ ጥቅም ላይ የዋለው ከ30 አስከ 40 በመቶ በመሆኑ ከ80 እስከ 90 በመቶ የሚሆነውን የኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ እንደሚገባ ተናግረዋል።

ሁለተኛው ማሻሻያ ለህዝብ ትልቅ ተስፋዎችን የያዘ በመሆኑ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚን ለመፍጠር የሚያስችል መሆኑን አስገንዝበዋል።

የሁለተኛው ሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው የ10 ዓመት የወደፊት ዕቅዶች ጋር የተሳሰረ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በመጀመሪያው ዙር ማሻሻያና ያልተሟሉ ሥራዎችን ለማሳካትና የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ሰፊ ሥራ ይከናወናል ሲሉ ተናግረዋል።

ሁለተኛው የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ የማክሮ ኮሚቴ፣ በገንዘብ እና በፕላንና ልማት ሚኒስትሮች የሚመራ የበይነ-ሚኒስትሮች አስተባባሪ ኮሚቴ እንዲሁም የተለያዩ ንዑሳን ኮሚቴዎችን የያዘ መሆኑንም ዶክተር እዮብ አመላክተዋል።

# ኢትዮጵያ በ78ኛው የተመድ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እየተካሄደ ይገኛል።

በተመድ የኢትዮጵያ ቋሚ መልዕክተኛ አምባሳደር ተስፋዬ ይልማ፤ ኢትዮጵያ በጉባዔው ያላትን ተሳትፎ አስመልክቶ በሰጡት ማብራሪያ ኢትዮጵያ ከጉባዔው ጎን ለጎን ከተለያዩ ሀገራት ጋር የሁለትዮሽ ውይይት ማድረጓን ገልጸዋል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ከተለያዩ ሀገራት ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ ከዓለም አቀፍ ተቋማትና አጋር አካላት ጋር በሁለትዮሽ፣ በቀጣናዊና በባለብዙ ወገን የትብብር ጉዳዮች ውይይት ማድረጋቸውን ተናግረዋል።

በዚህም ሀገራቱ ኢትዮጵያ የጀመረችው የለውጥ ጉዞና የሰላም ሂደት በትክክለኛ አቅጣጫ እየሄደ መሆኑን የጋራ መግባባት ተፈጥሮበታል ብለዋል።

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ በተለያዩ ሀገራትና ተቋማት በተዘጋጁ የጎንዮሽ የውይይት መድረኮች ተሳትፎ በማድረግ ያላትን አቋም ማስረዳቷንም ገልፀዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ማሻሻያ እንደሚያስፈልግና አፍሪካ በጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ መቀመጫ እንዲኖራት ድምጿን ማሰማቷን ተናግረዋል።

በተለይም በጠቅላላ ጉባዔው ኢትዮጵያ ያላትን እውነታ በሚገባ ማስረዳትና አቋሟንም በትክክል ማንፀባረቅ መቻሉን አመልክተዋል።

ከዓለም አቀፍ ተቋማትና የተለያዩ ኩባንያዎች ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ጋር የተደረጉ ውይይቶች ፍሬያማ መሆናቸውን አስረድተዋል።

ዓለም አቀፍ ተቋማት የፋይናንስ ድጋፍ ለማድረግና ኩባንያዎች በኢትዮጵያ መዋዕለ-ንዋያቸውን ለማፍሰስ ያሳዩት ፍላጎት ተስፋ ሰጪ መሆኑን ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ በሀገር አቀፍ፣ ቀጣናዊና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ያላትን ምልከታና አቋም የምታንፀባርቅበት የፖሊሲ ንግግር በጠቅላላ ጉባዔው ላይ እንደምታደርግ አስረድተዋል።

ከጉባዔው ጎን ለጎን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ከተመድ ዋና ፀሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ ጋር ውይይት አድርገዋል።

በወቅቱ ተመድ ከኢትዮጵያ ጋር ያለው ግንኙነት እንዲጠናከር በቁርጠኝነት እንደሚሰሩ የድርጅቱ ዋና ፀሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ ገልጸዋል።

በውይይታቸው ወቅት ዋና ፀሐፊው ኢትዮጵያ በባለ ብዙ ወገን የትብብር ሥርዓት ቁልፍ ሚና ያላት ሀገር ናት ብለዋል።

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ጥልቅ የሆነ የአጋርነት ስሜት እንደነበራቸው ጠቅሰው ኢትዮጵያ ያሉባትን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፈተናዎች ለመፍታት እያደረገች ባለው ጥረት ስኬታማ እንድትሆን ተመኝተዋል።

በአሜሪካ ኒውዮርክ እየተካሄደ ያለው 78ኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ እስከ መስከረም 15 ቀን 2016 ዓ.ም የሚቆይ ይሆናል።

# "የባሕልና የኃይማኖት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የጥላቻ አጀንዳ በመቅረጽ ብጥብጥና ረብሻ ሲፈጥሩ መቆየታቸውን አንስተው፤ አልፎ አልፎ በኢሬቻና በአንዳንድ በዓላት አከባበር ላይ ችግር ተፈጥሮ ሕይወትና ንብረት ሲጠፋ መቆየቱን ጠቁመዋል።

አሁን ላይ ግን ከፍተኛ ለውጥ መኖሩን የጠቀሱት አቶ ቀጄላ፤ ነገር ግን በኢትዮጵያ በሕዝቡ ዘንድ የባሕልና የኃይማኖት ልዩነት የፍቅር እንጂ የጥላቻ ምንጭ እንዳልሆኑ መታወቅ አለበት ብለዋል።

የትኛውም ባሕላዊም ሆነ ኃይማኖታዊ ኩነቶች ሲከበሩ ዓላማቸው ምስጋና፣ ሰላም፣ ፍቅርና አንድነት ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ በኢትዮጵያ ያለው እምቅ ባሕላዊና ኃይማኖታዊ ሀብቶች ለቆሙለት ዓላማ ካዋልናቸው እንደ ችግር የሚነሱት ጥላቻና መገፋፋት ቦታ እንደማይኖራቸው ተናግረዋል።

በዓላቱ ላይ ሕዝቡ በልዩነት ሳይገደብ ከየትኛውም ጊዜ በላይ ተቀራርቦ አብሮ መብላትና መጠጣት፣ ሃሳብ መለዋወጥ እና መደሰት እንደሚስተዋል ያነሱት አቶ ቀጀላ፣ እንዲህ ዓይነት ክስተቶች አንድነትና አብሮነትን ለማጎልበት እንደ መልካም አጋጣሚ እያገለገለ ይገኛል ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፣ ከሚታወቁት ባሕላዊ በዓላት ውጪ ገና የሚጠኑና ይፋ የሚደረጉ በርካታ እሴቶች አሉ። እንደ ሲዳማ፣ ወላይታ፣ ሐዲያ፣ ጎፋ እና የመሳሰሉት የራሳቸው የዘመን መቁጠሪያና የዘመን መለወጫ በዓል ያላቸው ሕዝቦች አሉ። ወደ ፊት የሕዝቦቹን ባሕል በማጎልበት ወደ እድል ለመቀየር በልዩ ትኩረት ይሠራል ነው ያሉት።

የሕዝቡን ባሕልዊና ኃይማት ማክበርና ማሳደግ በሕገመንግሥቱ የተቀመጠ ጉዳይ ቢሆንም ከሁሉም በላይ ግን ሕዝቡ በራሱ የሌላውን ለማክበር የሚያደርገው ጥረት የሚበረታታ መሆኑን አድንቀዋል። ይህ ሲባል ግን በልዩነቱ ውስጥ የሚታየውን ጠለቅ ያለውን አንድነት የሚጠሉ በጣት የሚቆጠሩ ፖለቲከኞች የሉም ማለት አይደለም ብለዋል።

ሕዝቡ መስቀል፣ መውሊድና እሬቻን ጨምሮ በዘንድሮ ዓመት የሚከበሩ ባሕላዊና ኃይማኖታዊ በዓላት እንደ ወትሮው በፍጹም ሰላም፣ ፍቅርና አብሮነት እንዲያከብርም ጠይቀዋል።

# እያገረሸ የሚገኘው የወባ ወረርሽኝ ስጋት

**አስናቀ ፀጋዬ**



የክረምቱ ወቅትን መገባደድ ተከትሎ የበጋ ወቅት ሲመጣ ሙቀት ስለሚኖር ለወባ ትንኝ መራባት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል። ለዚህም ነው ብዙ ጊዜ በዚህ ወቅት የወባ ወረርሽኝ እንዳይከሰት አስቀድሞ የመከላከል ሥራ የሚሠራው። በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች በነበሩ ግጭቶችና የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የወባ ወረርሽኝ እንዳይስፋፋ ትልቅ ስጋት አለ። ከዚህ አንፃር ማኅበረሰቡ ራሱን በወባ በሽታ ምክንያት ሊከሰት ከሚችል ህመምና ሞት እንዲጠብቅ ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ፣ በተለይ የሚዲያ ተቋማት ትልቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ይታመናል። ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትም እንደዚያው።

የጤና ልማትና ፀረ-ወባ ማኅበር ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ አክሊሉ ጌትነት እንደሚናገሩት፣ በመጪው ጊዜ የወባ ወረርሽኝ ሊከሰትና ሊስፋፋ እንደሚችል ስጋት አለ። ወባ በአመት ሁለት ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ይከሰታል ተብሎ ይታሰባል። አንደኛው የዝናብ ወቅት ከተገባደደ በኋላ መሆኑ ማኅበረሰቡ የወባ መቆጣጠሪያና መከላከያ መንገዶችን በአግባቡ፣ ሁልጊዜና በትክክል መከተል ይኖርበታል። ምን አልባት ደግሞ የወባ በሽታ ምልክቶችን ካየ ባስቸኳይ ወደ ሕክምና ቦታ በመሄድ አስፈላጊውን ሙያዊ እርዳታ ማግኘት ይጠበቅበታል። ለዚህም በወባ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር ዙሪያ ለኅብረተሰቡ አስፈላጊውን ግንዛቤ ማስጨበጥ ያስፈልጋል። ማኅበሩም እየሠራ ያለው ይህንኑ ነው።

ማኅበሩ በሃያ አምስት አመታት ጉዞው የወባ በሽታን በሚመለከት ለማኅበረሰቡ በከፍተኛ ደረጃ ግንዛቤ ሲያስጨብጥ ቆይቷል። በተለይ ደግሞ ወባ ገዳይ በሽታ እንደሆነና ትኩረትም እንዲያገኝ የጥብቅና ሥራ ሠርቷል። ካለፉት አምስት አመታት ወዲህ ደግሞ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ላይ በማተኮር የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል። በዋናነት ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች አጋላጭ ሁኔታዎች ላይ ትኩረቱን አድርጎ ይሠራል። ከሚሠራባቸው አጋላጭ ሁኔታዎች ውስጥ ደግሞ ትምባሆ፣ አልኮል፣ ጤናማ ያልሆኑ አመጋገቦችና የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎችን አለማድረግ ይገኙበታል።

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንደሚሉት፣ ባለፉት ሃያ አመታት የወባ ወረርሽኝ በከፍተኛ ደረጃ ቀንሶ ነበር። ባለፈው አመት ግን ወረርሽኙ 50 በመቶ እንደጨመረ መረጃዎች ያሳያሉ። ለዚህም የአየር ንብረት ለውጥና በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የተከሰቱ ግጭቶች፣ መፈናቀሎችና የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ዓይነተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል። የቁጥጥርና ክትትል ሥራዎች ላይም መዘናጋት ተፈጥሯል። ይህም በጥናት መለየትና ተረጋግጦ መውጣት ይጠበቅበታል። ወረርሽኙ የከፋ ጉዳት እንዳያስከትልም ማኅበረሰቡ የወባ መከላከያና መቆጣጠሪያ መንገዶችን በአግባቡ ተግባራዊ እንዲያደርግ ይጠበቃል። ማኅበሩም ይህንን መልዕክት በተለያዩ መንገዶች እያስተላለፈ ይገኛል።

የወባ ወረርሽኝ በዚህ አመት በከፍተኛ ደረጃ መጨመሩን መረጃዎች የሚያሳዩ በመሆናቸውና በቀጣይም ወረርሽኙ እንዳይስፋፋ ስጋት በመኖሩ የወረርሽኙን ስጋት ለመቀልበስ ማኅበረሰቡን በስፋት ማስተማር ያስፈልጋል። በሌላ በኩል ደግሞ ወባ ታክሞ የሚድን በሽታ ከመሆኑ አኳያ ቢቻል የወባ በሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ መንገዶችን በአግባቡ መተግበር ያስፈልጋል።

ለምሳሌ አጎበርን ሁልጊዜ በአግባቡ መጠቀም፣ በገጠር አካባቢዎች የወባ ትንኝ ማጥፊያ ኬሚካል ከተረጨ በኋላ በእበት ወይም በአመድ ግድግዳን አለመለቅለቅ፣ የወባ መራቢያ አካባቢዎችን ማዳረቅና የታቆሩ ውሃዎችን ማፋሰስ ይገባል። በሽታውና ለመከላከልና ለመቆጣጠር ሳይቻል ቀርቶ በበሽታው መያዝ ቢመጣ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ በአቅራቢያ ወደሚገኝ ጤና ተቋም በማምራት አስፈላጊውን ሕክምና ማድረግ ያስፈልጋል።

የጤና ልማትና ፀረ-ወባ ማኅበር መሥራችና ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አበረ ምህረቴ በበኩላቸው እንደሚናገሩት፣ ወባ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ከፍተኛ ተዛምዶ ያለው በሽታ ስለሆነ የአየር ንብረትና የወባ ባለሞያዎች ተገናኝተው መረጃ ቢቀያየሩና በጋራ ቢሠሩ ወረርሽኙን መተንበይ እንደሚያስችል በጥናት ለማረጋገጥ ተችሏል። ከሁለቱ ባለሞያዎች የተውጣጣ አንድ ግብረ ኃይልም ተቋቁሟል። ሁለቱ ባለሞያዎች በአንድ ላይ በመሥራታቸው ተሞክሯቸው ውጤታማ ነበር። በተለይ የአማራን ክልል ለአመታት በማጥናትና በተሞክሮነት በማየትና አመርቂ ውጤት ማግኘት በመቻሉ የባህርዳር ዩኒቨርሲቲና የአማራ ጤና ቢሮ በጋራ ለመሥራት ሥራውን ተረክበዋል።

አሁን ባለው ሁኔታ የወባ ወረርሽኝ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ሊከሰት እንደሚችል መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህ አንፃር ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በተቻላቸው አቅም ለኅብረተሰቡ የማስጠንቀቂያ ደወል ማሰማት ይኖርባቸዋል። በተለይ የፀጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ሕዝቦች አደጋ ውስጥ ሊገቡ ስለሚችሉ ሁሉም በጋራ ሊረባረብና ኅብረተሰቡን የማዳን ሥራ ሊሠራ ይገባል። በተለይ ደግሞ የሚዲያ አካላት ከሌሎች በተለየ በሽታውን በሚመለከት ኅብረተሰቡ የቅድመ መከላከልና መቆጣጠር ሥራ እንዲያከናውን የማስገንዘብ ኃላፊነት አለባቸው።

‹‹ማሌሪያ ኮንሰርቲየም›› በተሰኘ ዓለም አቀፍ ድርጅት የፀረ-ወባ ባለሞያ ሆነው የሚሠሩት ዶክተር አጎናፍር ተካልኝ እንደሚገልፁት፣ ወባ ድምፅ አልባ በሽታ ነው። በአብዛኛው እናቶችንና ሕፃናትን ያጠቃል። እ.ኤ.አ ከ2003 ጀምሮ በኢትዮጵያ በወባ በሽታ ምክንያት የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ቀንሶ ነበር። ይሁንና ባለፈው አመት በርካታ ሰዎች በወባ ምክንያት ሕይወታቸውን አጥተዋል።

በወሊድ ምክንያት አንድም ሴት መሞት የለባትም ተብሎ ትግል እየተደረገ እንደመሆኑ መጠን በወባ በሽታም አንድም ሰው ሕይወቱን እንዳያጣ ጠንካራ ሥራ መሠራት አለበት። መከላከል እየተቻለና ሕክምና እያለ በወባ ምክንያት ለምን ሰው እንደሚሞትና በአሁኑ ጊዜ ለምን የወባ ስርጭት እየጨመረ እንደመጣ ማጥናት ያስፈልጋል። በርግጥ ለወባ በሽታ ስርጭት እየጨመረ መምጣት አንዱ ምክንያት የአየር ንብረት ለውጥ ነው። በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በኢትዮጵያ የወባ ወረርሽኝ ከፍ ሊል ችሏል።

በሌላ በኩል ደግሞ የሕክምና አገልግሎት የተደራሽነት ችግር ተፈጥሯል። ይህም ማለት ግጭት በተፈጠረባቸው የሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች እንደልብ ገብቶ መድኃኒቶችንና የወባ መከላከያዎችን መስጠት አልተቻለም። በሌላ በኩል ደግሞ ሕክምና አገልግሎት መስጫ ግብአት እጥረት ይታያል። በተለይ የመድኃኒቶች፣ መመርመሪያ ኬሚካሎችና የባለሞያዎች እጥረት አለ። ይህም ለወባ ወረርሽኝ መስፋፋት የራሱን አስተዋፅኦ ያደርጋል።

የወባ ትንኝና ተህዋሲያኑ መላምድም ሌላው ከወባ ወረርሽኝ ጋር በተገናኘ የሚነሳ ችግር ሲሆን፣ ከዚህ ችግር ጋር በመጋፈጥ ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ይገኛል። በገንዘብ እጥረት ምክንያት የወባ ወረርሽኝን ለመቆጣጠር የሚያችሉ በርካታ ግብአቶች በጊዜው ሊደርሱ አልቻሉም። በባለሞያዎችም ሆነ በሚመለከተው ክፍል ትኩረት የመስጠት ችግር አለ። ይህም አንዱና ዋነኛው ሊሠራበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

> **‹‹ወባ በአመት ሁለት ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ይከሰታል ተብሎ ይታሰባል። አንደኛው የዝናብ ወቅት ከተገባደደ በኋላ መሆኑ ማኅበረሰቡ የወባ መቆጣጠሪያና መከላከያ መንገዶችን በአግባቡ፣ ሁልጊዜና በትክክል መከተል ይኖርበታል። ምን አልባት ደግሞ የወባ በሽታ ምልክቶችን ካየ ባስቸኳይ ወደ ሕክምና ቦታ በመሄድ አስፈላጊውን ሙያዊ እርዳታ ማግኘት ይጠበቅበታል። ለዚህም በወባ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር ዙሪያ ለኅብረተሰቡ አስፈላጊውን ግንዛቤ ማስጨበጥ ያስፈልጋል።››**

ከግጭትና ከፀጥታ ችግር ጋር በተያያዘ ደግሞ የሕዝቦች መፈናቀል አለ። ለተፈናቃዮች በወባ በሽታ እንዳይጠቁ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ አይደለም። በዚሁ መነሻነት ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመሆን በቀጣይ ተፈናቃዮችን ትኩረት ያደረገ የወባ መከላከል ሥራ ለመሥራት ታቅዷል።

በእነዚህና መሰል ምክንያቶች በኢትዮጵያ የወባ ወረርሽኝ እየጨመረ መጥቷል። በቀጣይም ወረርሽኙ እንዳይስፋፋ ስጋት አለ። ከዚህ አንፃር ስጋቱን ለመቀልበስ ከአንዱ በስተቀር ለሁሉም መፍትሔ ይኖራል። ይኸውም የአየር ንብረት ለውጥ ነው። የአየር ንብረት ለውጥ ለሚያመጣቸው ችግሮች ግን መፍትሔዎችን ማስቀመጥ ይቻላል።

በይበልጥ ኅብረተሰቡ የተዘናጋ እንደመሆኑና በወቅቱ አጎበርን የመሳሰሉ የወባ በሽታ መከላከያዎችን የማይጠቀም በመሆኑ፤ እንዲሁም፣ የበሽታውን ምልክት ሲያዩ በአስቸኳይ ወደ ጤና ተቋም ስለማይሄዱ የወባ በሽታ ስርጭት ከፍ እንዲል የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል። ከዚህ አንፃር በተለይ መገናኛ ብዙኃን የወባ በሽታ መከላከያና መቆጣጠሪያ መንገዶችን በሚመለከት ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ከዚህ ባለፈ የወባ በሽታ አጀንዳ እንዲሆንና ሁሉም ሰው ትኩረት እንዲሰጠው የጤና ልማትና ፀረ ወባ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ መደገፍና ማበረታታት ከሁሉም ይጠበቃል።

ወባና ትንኝ ወለድ በሽታዎች በአፍሪካ አሳሳቢ እየሆኑ ስለመምጣታቸው በዚህ ሳምንት መግቢያ ላይ የአፍሪካ ወባና ትንኝ ቁጥጥር ማኅበር /PAMCA/ በአዲስ አበባ በተካሄደው ዘጠነኛ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ መነገሩ ይታወሳል። በዚሁ ጉባኤ ወባና ትንኝ ወለድ በሽታዎችን በሚመለከት በርካታ ጉዳዮች ተነስተዋል። በተለይ አፍሪካ በርካታ ችግሮች ያሉባትና ከበሽታዎች ጋር በተያያዘም በርካታ ጫና እንዳረፈባት በቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች አማካኝነት በጉባኤው ተነግሯል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በዓለም አቀፍ ደረጃ አለ የሚባለው የወባ በሽታ ከ90 በመቶ በላይ በዚሁ የአፍሪካ አህጉር መሆኑ ተገልጿል። የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖም ለወባ በሽታ ጫና ዓይነተኛ አስተዋፅኦ ማድረጉ ተጠቁሟል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በጉባኤው ኢትዮጵያ በጤና ሚኒስትሯ ዶክተር ሊያ ታደሰ አማካኝነት ከዚህ ቀደም የወባ ስርጭትን ለመቀነስ ሰፊ ሥራ ሲሠራ መቆየቱንና እ.ኤ.አ በ2020 በሽታው ገዳይ እንዳይሆን መቆጣጠር መቻሉ ተጠቁሟል። ይሁንና ካለፉት ሦስት አመታት ወዲህ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖን ተከትሎ የወባ በሽታ እንደ አዲስ እያገረሸ መሆኑ ተነግሯል። ወባ ብቻ ሳይሆን ትንኝ ወለድና ሌሎች ወባ መሰል በሽታዎች እየተከሰቱ ስለመሆናቸው ተገልጿል። ለአብነትም ዴንጌ፣ ችኩንጉኛ (ቅልጥም ሰባሪ)፣ የሎ ፊቨር የተሰኙ የበሽታ ዓይነቶች በኢትዮጵያና በሌሎችም የአፍሪካ ሀገራት እንደገና እየታዩ መሆናቸው ተጠቅሷል።

በዚህም የወባ ወረርሽኝ በኢትዮጵያም ሆነ በአፍሪካ እየጨመረ ስለመምጣቱ ተጠቁሟል። ከዚህ ቀደም የሚታወቀው የወባ ትንኝ የነበር ቢሆንም አሁን ላይ ግን Anopheles stephensi የተሰኘች የወባ ትንኝ ዝርያ በኢትዮጵያና በሌሎች የአፍሪካ ሀገራት እ.ኤ.አ በ2016 ስለመከሰቷ ተነግሯል። ይህች ትንኝ በተለየ ሁኔታ በሽታውን በከተሞች አካባቢ ማስፋፋቷ ደግሞ አደገኛነቷን እንደሚያሳይ ተመላክቷል። ይህንን ለመቆጣጠር ታዲያ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን በጉባኤው ተጠቅሶ፣ ነገር ግን ሥራው በቂ ባለመሆኑ አጠናክሮ መሥራት እንደሚያስፈልግ መግባባት ላይ ተደርሷል።

# ተናጋሪው ዶሴ

## የቀን ጎዶሎ

ምሕረት ሞገስ

መስፍን ኩሳ እና አዲስ ግዛው ጓደኛሞች ናቸው። ሁለቱም ኑሯቸው ጎዳና ላይ መሆኑ፤ አብረው መራባቸው እና አንድ ላይ መብላት መጠጣታቸው ይበልጥ አቀራርቧቸዋል። ሐምሌ 9 ቀን 2012 ዓ.ም እሁድ መሆኑን ተከትሎ፤ ሁለቱም መዝናናት ፈልገዋል። ማደሪያቸው አዲስ አበባ ከመስቀል አደባባይ በስተግራ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን አቅራቢያ መኪና ማጠቢያው አካባቢ ሲሆን፤ በዕለቱ ብዙም ሳይርቁ ጠጅ መጠጣት ፈለጉ።

በግምት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሲሆን፤ ከፍላሚንጎ ጀርባ ወዳለው ጤናዳም ጠጅ ቤት ገብተው ሁለት ሁለት ብርሌ ጠጅ ጠጡ። የጠጡበትን ሂሳብ መስፍን ከፍሎ ወደ ማደሪያቸው ሲሔዱ፤ ከእስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት የአውቶቡስ ፌርማታው ወንበር ላይ በስምም ሆነ በመልክ የማያውቁት መካከለኛ ቁመት ያለው ሰው ተቀምጦ አገኙ። ሰውየው ለአዲስ ግዛው ሰላምታ ሰጠ። አዲስ ግዛው ግን ለቀረበለት ሰላምታ ምላሽ አልሰጠም። በሌላ በኩል መስፍን ኩሳ ለአዲሱ ሰው ሰላምታ አቀረበ፤ አዲሱ ሰው ግን መስፍንን ለማነጋገር አልፈለገም። ትተውት «ወደ ማደሪያችን እንሂድ» ተባብለው ከአካባቢው ዘወር አሉ።

### ሴላኛው የጎዳና ሳይ ነዋሪ ዳንኤል ኃይሉ

ዳንኤል ኃይሉ በ1990 ዓ.ም ከአቶ ኃይሉ ተፈራ እና ከወይዘሮ ብርቱካን ወልደኪዳን በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን አቦምሳ ቀበሌ ውስጥ ተወለደ። በአቦምሳ ትምህርት ቤት ከ1996 እስከ 2004 ዓ.ም 8ኛ ክፍል እስከሚደርስ ትምህርቱን ተከታትሏል። አባቱ ሕይወታቸው ማለፉን ተከትሎ ትምህርት ያቋረጠ ሲሆን፤ ራሱን ለመቻል ወደ ንግድ ሥራ ገብቶ ነበር። ነገር ግን ሊሳካለት አልቻለም። በ2007 ዓ.ም ሕይወትን በተሻለ መልኩ ለመምራት ያመቻል ብሎ ወዳመነባት ወደ አዲስ አበባ ከተማ ለመግባት ወሰነ። አስቦም አላበቃ ተሳፍሮ አዲስ አበባ ገባ።

አዲስ አበባ ከተማ ላይ መኖር እንደገመተው ቀላል አልነበረም። ማደሪያ ማግኘት እና የሚቀምሰውን ጎርሶ ማደር አዳጋች ሆነ። ውሎ እና አዳሩን ጎዳና ላይ አደረገ። በጎዳና ሕይወቱ ከሌሎች የጎዳና ነዋሪዎች ጋር መጋጨት የተለመደ ነው። እሁድ ሃምሌ 9 ቀን 2012 ዓ.ም ብርድ ብርድ ሲለው ከወንድማማቾች ጠጅ ቤት ጠጅ ገዝቶ፤ እስጢፋኖስ በር ላይ ያለው የአውቶቡስ ፌርማታ ስር ተቀምጦ ሲጠጣ መስፍን ኩሳ እና አዲስ ግዛው ወደ እርሱ ተጠጉ። እርሱም ለጊዜው በአይኑ ገርምመውት እርሱም አተኩሮ አይቷቸው አለፋት።

### ምሽት አምስት ሰዓት

መስፍን ከጓደኛው ጋር ጠጅ ጠጥተው ወደ ማደሪያቸው ሲገቡ ራበው። አጠገባቸው ሽራ ወጥሮ ወደሚተኛው ጓደኛቸው ምግብ ሲጠይቅ፤ አያሌው ደምሴ በቅፅል ስሙ ራስታው የተሰኘው ሌላኛው የጎዳና ላይ ነዋሪ ጎረቤታቸው የሚበላ አምጥቶ ለእነርሱም በጥቁር ፌስታል እንዳስቀመጠላቸው ነገራቸው። ሁለቱም ‹‹መኝታችንን አመቻችተንና አልጋ አነጣጥፈን፤ እንበላለን።›› ተባብለው የተቀመጠላቸውን ምግብ በጥቁር ፌስታል በራቸው ላይ አስቀምጠው ሁለቱም በሸራ ወደ ተወጠረው ማደሪያቸው ገቡ። መስፍን አልጋውን አስተካክሎ ጨርሶ ሲወጣ፤ ጓደኛውን አላገኘውም። የጓደኛውን ስም ቢጠራም ምላሽ የሚሰጠው አጣ። ርቦታል ለመብላት እየተቻኮለ ጓደኛውን ፍለጋ ሲዟዟር ወደ ቤተክርስቲያኑ ተመለከተ። ጓደኛው አዲስ አውቶቢስ ፌርማታው ጋር ሔዶ ቀድሞ ካገኙት ሰው ጋር እየታገለ መሆኑን ተመለከተ።

### ዳንኤል በዛች ሰዓት

ዳንኤል ብርድ ተጫጭኖታልና በሃይላንድ የያዘውን ጠጅ እየተጎነጨ ብቻውን ሲተክዝ፤ በአይን የሚያውቀው እና ስሙን በውል የማያውቀው ከጓደኛው ጋር በዓይኑ ገርምሞት ያለፈው አዲስ ግዛው ከመኪናው ማጠቢያ በኩል ወደ እርሱ ሲጠጋ



**አ**ዲስ አንዴ ደረቱ አካባቢ በመውጋቱ ወዲያው መሬት ላይ ሲወድቅ የተመለከተ ጓደኛው መስፍን፤ ተንደርድሮ ተጠግቶ ዳንኤልን በቡጢ ለመምታት ሰነዘረ

ተመለከተ። አዲስ እየቀረበው ሲመጣ ረዥም የእንጨት እጄታ ያለው ቢላዋ ይዞ ነበር። ዳንኤል አጠገብ መጥቶ ሲቀመጥ፤ ዳንኤል ሁኔታው ስላላማረው ተነስቶ ወደ ማደሪያው ወደ ድልድዩ ሲያመራ አዲስ ከኋላው ቢላዋውን ሰነዘረበት። ዳንኤል የተሰነዘረው ቢላዋ ሰውነቱ ጋር ከመድረሱ በፊት በመጠራጠሩ ዞሮ መታገል ጀመሩ። ዳንኤል ቢላዋውን መቀማት ቻለ። ዳንኤል ራሱን ለመከላከል ቢላዋውን ነጥቆ በድንጋጤ አዲስን ደረቱ ላይ ወጋው።

አዲስ አንዴ ደረቱ አካባቢ በመውጋቱ ወዲያው መሬት ላይ ሲወድቅ የተመለከተ ጓደኛው መስፍን፤ ተንደርድሮ ተጠግቶ ዳንኤልን በቡጢ ለመምታት ሰነዘረ። ሆኖም ዳንኤል በመስፍንም የሚመታ ዓይነት አልሆነም፤ የተሰነዘረበት ቡጢ ፊቱ ላይ እንዳያልፍ ተከላክሎ በድንጋጤ በድጋሚ አዲስን በወጋበት ቢላዋ መስፍንን ወጋበት። ዳንኤል ሁለቱም ላይ ጉዳት ካደረሰ በኋላ ደማቸው እየፈሰሰ ሲያይ፤ ሌሎች ሰዎች መጥተው እንዳያጠቁት በመስጋት ቢላዋውን እዛው ጥሎ ከማደሪያው በተቃራኒ አቅጣጫ ወደ ማስቀል አደባባይ ሮጠ።

### የድረሱልኝ ጥሪ

መስፍን በበኩሉ የድረሱልኝ ጥሪውን በጩኸት ቢያስተጋባም፤ የመጣለት አልነበረም። ጓደኛው በጣም ተወግቶ ስለወደቀ እርሱን የሚያድነውን ለማፈላለግ ደሙን እያፈሰሰ ምግብ ወደ ሰጣቸው ጓደኛቸው ወደ አያሌው ደምሴ (ራስታው) ሔደ። እንቅልፍ ላይ የነበረው ራስታውን ቀሰቀሰው። ነገር ግን ራስታው እግሩን ታሞ ስለነበር፤ አዲስን ሃኪም ቤት መውሰድ አልችልም አለ። ሌላ ሰው ማግኘት ባለመቻላቸው፤ መስፍን ጓደኛው አዲስ እንዳይሞት በመስጋቱ ‹‹እንደምንም አሸክመኝ፤ እኔ እሸከመዋለሁ›› ብሎ መስፍን ጓደኛውን አዲስን ተሸክሞ ወደ ሃኪም ቤት ለመውሰድ ጥረት አደረገ።

ነገር ግን መስፍንም በመወጋቱ ጓደኛውን ተሸክሞ መጓዝ አልቻለም። ሲያቅተው አዲስን አስፓልት ላይ አስተኝቶ መጮህ ጀመረ። መስፍን እና ራስታው ጓደኛቸውን አዲስን አስፓልት ላይ አድርገው ቆመው ግራ ተጋብተው ሲያማትሩ በፓትሮል የሚዞሩ ፖሊሶች አገኙዋቸው። ሁለቱንም ወደ መሿለኪያ ጤና ጣቢያ ወሰዷቸው። በግምት ከምሽቱ 5 ሰዓት ከ30 ላይ በስለት የተወጋው አዲስ ስድስት ሰዓት ለመሆን አስር ደቂቃ ሲቀረው ህይወቱ አለፈ። ገዳይ ዳንኤል ኃይሉ አልተገኘም።

### የመስፍን ኩሳ የምስክርነት ቃል

ከአቶ ኩሳ ሳዴቦ እና ከታሪኬ ወርቅነሽ በ1990 ሐዋሳ ከተማ 03 ቀበሌ የተወለደው መስፍን ኩሳ፤ በሐዋሳ ቤተልሔም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተምሯል። የእናቱን ሞት ተከትሎ ትምህርት ያቋረጠው መስፍን፤ እስከ 2011 ዓ.ም እዛው ሐዋሳ ከተማ ላይ የጎዳና ሕይወትን ሲገፋ ቆይቷል። በ2012 ዓ.ም መስከረም ወር ላይ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በጎዳና ላይ መኖር የጀመረው ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ባንቢስ አካባቢ ነበር። ባንቢስ አካባቢ ብዙም ስላልተመቸው በዛው ክፍለ ከተማ እስጢፋኖስ አካባቢ ሸራ ወጥሮ መኖር ጀመረ።

አዲስ አበባ መጥቶ አንዳንዴ ሥራ ሲያገኝ የቀን ሠራተኛ ሆኖ ሕይወቱን ሲገፋ፤ አዲስ የሚባል ጓደኛ አገኘ። ሁለቱም ጓደኛሞች አብረው በጎዳና ላይ ሕይወታቸውን ሲገፉ፤ ልብስ ተቀያይረው እየለበሱ፤ አብረው እየጠጡ እና አብረው እየበሉ ነበር። በተለይ መስፍን እንደሚለው አንዳንዴ ብርድ ለመከላከል ጠጅ ይጠጣሉ። እሁድ ሐምሌ 9 ቀን 2012 ዓ.ም እንደለመዱት ጠጅ ጠጥተው ወደ ማደሪያቸው ተመለሱ።

በግምት ከምሽቱ 5 ሰዓት ተኩል አካባቢ፤ መስፍን ከጓደኛው አዲስ ጋር ምግብ ለመብላት ሲጠራው አላገኘውም። እርሱ መኪና ማጠቢያው አካባቢ ሆኖ ወደ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ሲመለከት፤ ጓደኛው አዲስ ከማያውቀው ሰው ጋር ሲታገል አየ። ይህን የተመለከተው መስፍን እየሮጠ ወደ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን አቅጣጫ ሲሔድ፤ በግምት 10 ሜትር ሲቀረው በመስፍን ያልታወቀው ሰው (ዳንኤል ሃይሉ ) አዲስን በግራ በኩል ደረቱን ወጋው።

አዲስ ወደቀ፤ መስፍን ጓደኛውን ለመርዳት ዳንኤል ሃይሉ ጋር እንደደረሰ እጁን ጨብጦ ቡጢ ሰነዘረ፤ ዳንኤል በመስፍንም የሚመታ ዓይነት አልነበረም። የተሰነዘረበትን ቡጢ አምልጦ በቀኝ እጁ የመስፍንን ግራ ጎን ቀበቶ ማሰሪያው አካባቢ ወግቶት ወደ መስቀል አደባባይ ሮጠ። መስፍን ከራስታው ጋር ተባብሮ አዲስን ለማሳከም ጥረት ቢያደርግም የአዲስ ሕይወት አለፈ።

መስፍን በምስክርነት ቃሉ ላይ እንዳብራራው፤ አዲስ መሞቱን ተከትሎ ለምርመራ ሆስፒታል ሲሔድ፤ መስፍን ኩሳ ደግሞ የህክምና እርዳታ ተደርጎለት ተሻለው። ነገር ግን በመጨረሻም መስፍን ጓደኛህ አዲስን ከተኛበት አስነስተህ ራት እንብላ በሚል ሰበብ ከማደሪያው አርቀህ በጋራ በምትጠቀሙበት ቢላዋ ገድለህዋል በሚል በሰው መግደል ወንጀል ተከስሶ እስር ቤት ገባ።

### የዳንኤል ኃይሉ የዕምነት ክህደት ቃል

ዳንኤል አዲስን እና መስፍንን ከወጋ በኋላ ከአካባቢው ተሠወረ። ዳንኤል እንደተናገረው፤ ድርጊቱን የፈፀመው ራሱን ለመከላከል ሲል ነው። ራሱን በመከላከል ሒደት ውስጥ የፈፀመው ድርጊትም ሕይወት እስከማጥፋት ይደርሳል ብሎ አልገመተም። ወደ አካባቢው ሲመለስ ግን የሰማው ዜና አስደንጋጭ ሆነበት። እርሱ በቢላዋ የወጋው አዲስ የመሞቱን ዜና ሲሰማ ያለማንም አስገዳጅ ህዳር 6 ቀን 2013 ዓ.ም በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ በመሔድ እጁን ሰጥቷል።

ዳንኤል የዕምነት ክህደት ቃሉን ሲሰጥ ከአዲስም ሆነ ከመስፍን ጋር የሚያጋጨው ምንም ምክንያት አልነበረውም። አዲስን በዓይን ከማወቅ ውጪ መስፍንን እንደውም አይቶት አያውቅም፤ በአጋጣሚ ያለምንም ምክንያት አዲስ ሽንኩርት መክተፊያ ቢላዋ ይዞ ሊወጋው በመሞከሩ ራሱን ለመከላከል ባደረገው ጥረት ሁለቱም ላይ ጉዳት አድርሷል። ይህንንም አምኖ ለፖሊስ ቃሉን ሰጥቷል።

### የፖሊስ ምርመራ

በቅድሚያ አዲስ ህይወቱ ማለፉን ተከትሎ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን መርማሪና የፎቶግራ ባለሞያ በአምቡላንስ መኪና ቦታው ላይ በመድረስ አስከሬኑን ባለበት ሁኔታ ፎቶ አነሱ። በመቀጠል አስከሬኑ ለምርመራ ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ህክምና ኮሌጅ የተወሰደ ሲሆን፤ መስፍንም የሕክምና ዕርዳታ ተደረገለት።

ምንም እንኳ የመጀመሪያው ተጠርጣሪ መስፍን ኩሳ ቢሆንም፤ ተከሳሽ ዳንኤል ሃይሉ ሕዳር 6 ቀን 2013 ዓ.ም በገዛ ፍቃዱ እጁን በመስጠቱ እና ወንጀሉን መፈፀሙን በማመኑ እስር ቤት ገባ። ፖሊስም ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል የተፃፈ የአስከሬን የምርመራ ውጤት፤ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ራስ ደስታ ሆስፒታል ጤና ቢሮ የተፃፈ የአቶ መስፍን ኩሳ የህክምና ማስረጃ፤ የሟች አስከሬን እና ወንጀሉ የተፈፀመበትን ቦታ ለማሳየት የተነሳ ፎቶ ፤ ሶስት የሰው ምስክር አያይዞ በዕለቱ ማለትም በሐምሌ 9 ቀን 2012 በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ወንጀል መፈፀሙን የሚያሳይ ማስረጃ በማደራጀት ፖሊስ ለአቃቤ ህግ አቀረበ።

አቃቤ ህግም የ29 ዓመቱ ዳንኤል በሐምሌ 9 ቀን 2012 ዓ.ም እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ተብሎ በሚጠራው አካባቢ፤ ሟች አዲስ ግዛውን በቢላዋ ደረቱ ላይ ወግቶታል። አቶ አዲስ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል። ዳንኤል ከዚህ ተራ የግድይ ወንጀል በተጨማሪ፣ በአቶ መስፍን ኩሳ ላይም በተመሳሳይ መልኩ በቢላዋ ታፋውን ወግቶ ደሙን በማፍሰሱ እና በማቁሰሉ በቀላል የአካል ጉዳት የማድረስ ወንጀል ሊጠየቅ ይገባል ሲል አቃቢ ህግ ክስ መስርቶበታል።

### ውሳኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድቤት በጥር 26 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክስ እና ማስረጃውን ከሕግ ጋር አገናዝቦ በሰጠው ውሳኔ፤ ዳንኤል ኃይሉ በፈፀመው የሰው መግደል ወንጀል የ14 ዓመት ፅኑ እስራት ይገባዋል ሲል ፈርዶበታል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ስለ ነገው ምን ታስቧል?

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

የአንዳንዱ ሰው ግዴለሽነት ከማስገረም አልፎ ያናድዳል። ነገ ሌላ ቀን አይመስለውም። ውሎ አድሮ ስለሚከተል ችግር ፣ ስለሚኖር ተጽዕኖ አንዳች አያስብም።፡ ባገኘው አጋጣሚ ያሻውን ይናገራል። ምስሉን ፣ ፎቶውን በፈለገው መልኩ አዘጋጅቶ ለሚፈልጋቸውና ለማይፈልጉት ጭምር ያሰራጫል።

እንዲህ ሲባል ጉዳዩ በዚህ ብቻ ይቋጫል ማለት አይደለም። ከሚለቀቀው ምስል ጋር አባሪ የሚሆን አስገራሚ መልዕክት አይጠፋም። የኔ ርዕሰ ጉዳይም ይኸው ነው። ምስላቸውን ከአጓጉል መልዕክት ጋር ለጥፈው ‹‹ስሙን፣ ጉዳያችንን እዩልን›› ብለው ነውራቸውን ስለሚያጋሩን አንዳንዶች።

መቼም ይህ ማህበራዊ ሚዲያ ይሉት አያሳየን የለም። ከራስ ታሪክ ጀምሮ እስከሌሎች ጉድ ያስቃኘናል። ይህ አጋጣሚ ምስጢርና ነውር ስለሚባሉት እውነታዎች የሚጨነቅ አይደለም። ባለቤቱ የማያውቀውን ጉድ አውጥቶ ከአደባባይ ማስጣት ልማዱ ነው። አንዳንዶች በዚህ ማህበራዊ ሚዲያው አያምኑም። ተሳትፎው የላቸውም። ስማቸው በፌስ ቡክ ፣በቲክቶኩ መንደር አይነሳም። እንደውም ብዘዎቹ የሌሎችንም ገጽ ገልጦ የማየት ልምዱን ትተውታል። በእነሱ እሳቤ ይህን ማድረጉ ቢጎዳ እንጂ አይጠቅምም።

እንዲህ አይነቶቹ ወገኖች ታቅቦ መቀመጥን እንደ አማራጭ ቢወስዱትም ‹‹እናውቃችኋለን›› ባዮቹ ደግሞ ላይተዋቸው ይችላሉ። ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ተጠቅመው ስማቸውን ያጠፉሉ ፣ ታሪካቸውኝ ያጎድፉሉ። ታዲያ ይህ ሁሉ ዘመቻ የሚካሄድባቸው ተጠቂዎች የሆነባቸውን በደል ላያውቁት ሁሉ ይችላሉ።

ስማቸው ስለመነሳቱ ከሌሎች በሚነገራቸው ጊዜ ግን እጃቸውን አጣጥፈው አይቀመጡም። ምላሽና ማስተባበያውን ሊሰጡ ‹‹አለን›› ማለታቸው አይቀሬ ይሆናል። በዚህ ሰበብ ሳያስቡት ከዚህ መንደር ዘልቀው ቤተኛ ይሆናሉ። በስድብና በጥላቻ የተለጠፈባቸውን ስም ለመፋቅ ሲሊ ምላሽ ከሚዲያው መንደር ከርመውም የልማዱ ሱሰኛ ሆነው ይዘልቃሉ።

እንዲህ አይነቶቹን በርካታ አጋጣሚዎች ምሳሌ እየመዘዙ ማንሳት ይቻላል። ለዛሬው ግን እያስገረመኝ ስላለው አንድ እውነት ላነሳና ልታዘብ ግድ ብሎኛል።

በቅርብ ጊዜ ነው። ከአንድ የዩቲብ ሚዲያ ጋዜጠኛ ጋር ቃለመጠይቅ የሚያደርግ አንድ ግለሰብ አትኩሮት በሰጠበት ርዕሰ ጉዳይ ጋር ትልቅ ውይይት ያደርጋል። የተነሳው ርዕስ የቤተሰብ ብሎም የባልና ሚስት ግንኙነት በመሆኑ በርካቶች እየተከታተሉት ነው። ጋዜጠኛው ይጠይቃል ። ግለሰቡ ፊቱ ሳይሸፈን ፣ድምጹ ሳይደበቅ ስለሚስቱ ገበና አንድ በአንድ ይዘረዝራል።

ወዳጆቼ! ልብ በሉልኝ እየተነሳ ያለው ጉዳይ ስለ ባልና ሚስት ነው። ተናጋሪው ደግሞ በግልጽ ማንነቱ ይታያል። የማን ባል፣ የነማን አባት እንደሆነ ነጋሪ አያሻውም። በዚህ ጥላ ስር የተገነባው ቤተሰብ የሚባል ትልቁ ተቋም ህልውናው የታሰበበት አይመስልም። ሰዎች በቤታቸው በግል አልያም በምስጢር ሊያነሱት የሚገባው ጉዳይ የባቄላ ወፍጮ ሆኖ መከካት መበካት ተይዟል።

ጋዜጠኛው አሁንም ይጠይቃል። በሚስቴ ተበድያለሁ ባዩ አባወራ የጀመረውን የቤቱን ገበና እንደክር ይተረትራል። የሚወራው ጉዳይ የተለመደው የቤት ወጪ፣ የቅናትና ጠብ ነገር አይምሰላችሁ ። ያለነውር እየተዘከዘከ ያለው የባልና ሚስቱ የፍቅር ግንኙነት ነው።

እንዲህ ስላችሁ ጉዳዩ በቃላት ብቻ አይወሳም። በሁለቱ ይሁንታ ሊቀር የሚገባው የአልጋ ላይ ጥምረት በግልጽ ተገልጦ ፀሀይ እንዲሞቀው፣ ሁሉም እንዲያውቀው እየሆነ ነው። ውይይቱ ጥንዶቹ ከሁለት አስር ዓመታት በላይ በዘለቁበት የትዳር ጎጆ የነበራቸውን ግንኙነት በገሀድ አውጥቶ ያሳያል።

በቆዩባቸው ጥቂት የማይባሉ የትዳር ዓመታት በቁጥር የተወሰነውን የፍቅር ግንኙነታቸው እያሰላ ውጤቱ አንሷል ፣ሳስቷል በሚል እሳቤ በግልጽ ይፈርዳል። ይህን ውይይት የሚከታተሉ ተመልካቾች ደግሞ ሰውየውን ደግፈው ሚስቲቱን አነውረው ያሻቸውን ይላሉ።

በጣም የሚገርመው ነገር በዚህ መሀል ሊታሰብበት የሚገባው የልጆችና የመላው ቤተሰብ ጉዳይ ከምንም ያለመጣፉ ነው። ይህ እውነታ የሚዲያ ፍጆታ ከሆነ በኋላ የሚረሳ የሚዘነጋ ነው። ምንአልባትም የአንድ ሰሞን ግርምታን አጭሮ ርዕስ ከመሆን ይፋቃል። በእኔ ዕምነት ግን በሚመለከተው አካል አእምሮ አሳርፎ የሚያልፈው የበደል ጫና በቀላሉ አይታይም።

በተለይ ደግሞ የጉዳዩን ባለቤት በእጅጉ ያሸማቅቃል። በአካል ተገኝቶ ምላሽና ማስተባበያ በማይሰጥበት አጋጣሚ ስሙ መብጠልጠሉ ጉዳቱን ከፍ የሚያደርግ ስብራት ያስከትላል። እንደ ግለሰብ ጥንካሬው ካለ ግን በህግ መጠየቅና መክሰስ ጭምር ይቻል ይመስለኛል። ብዙ ጊዜ ግን በተለይ በቤተሰቦች መሀል እንዲህ ማደረጉ ላይ አልተለመደም።

በዚህ መሰሉ ውይይት መሀል ማንነታቸው በግልጽ የሚታወቁ ልጆች በባልንጀሮቻቸው ዘንድ ጥርስ ውስጥ መግባታቸው አይቀርም። የእከሊት እናት አባት፣እህት፣ ወንድም እየተባለ ስማቸው በእኩል ይነሳል። ይህ ክፉ አጋጣሚ ደግሞ እንደሚጠቀሰው የውይይት ርዕሰ ጉዳይ ይወሰናል። ልጆቹ በዚህ አጋጣሚ ነውርነቱን ፣አሳፋሪነቱን በእኩል መጋራታቸው አይቀሬ ነው።

አንዳንዴ አንዳንድ ሰዎች በቤታቸው ያልፈቱትን ችግር ከሚዲያው አምጥተው ‹‹ፍረዱኝ›› ሲሉ ይሰማል። በእኔ ግምት እንዲህ ማድረጋቸው ለሌሎች መጠቀሚያ ካልሆነ በቀር ስለነሱ ኢምንት ታህል ፋይዳ አይኖረውም።

በግልጽ የሚወጣውን ምስጢር በእኩል የሚጋሩ ተመልካቾች ደግሞ ሁሉም እኩል እሳቤ የላቸውም። አንዳንዶቹ የአንዱን ወገን ይዘው ሚዛን አልባ ሃሳብ ይሰጣሉ። ሌሎቹ ደግሞ ይባስ ብለው በስድብ ያጥረገርጋሉ። ከፊሎቹም ‹‹እናውቃለን›› በሚሉት ሌላ ምስጢር ተሳትፈው እሳት ለማቀጣጠል ይፈጥናሉ።

እንደ እኔ ዕምነት አብሮን የቆየው የሽምግልና ባህላችን በማህበራዊ ሚዲያው ሲሸሞነሞን አልኖረም። በጥንዶች መሀል ችግር ቢኖር በቤተዘመድ ጉባኤ መፍታቱ ተለምዷል። ‹‹አንተም ተይ ፣ አንተም ተው›› ይሉት ልማድ የጠበቀ ቋጠሮን ለመፍታት አቅም አያንሰውም።

እንዲህ አይነቱ የባልና ሚስት ችግር ሲፈታ የቆየው በፌስቡክ፣በቲክቶክና በዩቲዩብ ገጾች አልነበረም።እንዲህ በሆነ ጊዜ ‹‹በድያለሁ፣አልያም ተበድያለሁ›› የሚል አካል ዕምነት ሃይማኖቱ ጭምር ለመፍትሄው ይጠቀማል። በልጆቹ፣ በጎረቤቶቹ ይዳኛል። እንደዘንድሮ ፍርድ ውሳኔው የሚሰጠው በማህበራዊ ሚዲያ አይደለም። ‹‹ጉዳዩ ጉዳያችሁ›› ያሉ ወዳጆች፣ምስጢርን ድብቅ ፣ሽሽግ አድርገው መፍትሄውን ይሰጣሉ። ጠብን አርቀው ፍቅርን ያወርሳሉ።

አሁን ላይ ግን ይህ ሁሉ እውነታ ከስጋት እየወደቀ ነው። የቤተሰብ ምስጢር ፣ ገበና ይሉት የለም። ነውር ፣ ህጋዊ ሆኖ ካደባባይ ወጥቷል። የአንዱን ቤት ገበታ የሚቆርሰ ው፣የሚቦጠቡጠው የማህበራዊ ገጽ ዕድርተኛው እየሆነ ነው።

ይህ ክፉ ጅማሬ ሊቆም ይገባል።ስለነገ ህይወት፣ስለልጆች ሞራልና ማንነት ማሰብ መጠንቀቅ የግድ ነው። ‹‹የሚያልፍ ዝናብ አይምታህ፣ ‹የሚያድግ ልጅ አይጥላህ፡›› ይሉት ተረት ያለነገር አልተባለምና ልቦና ይስጠን።

## ዓለም አቀፍ



### የሱዳን ተፋላሚ ኃይሎች በተመድ ስብሰባ እርስበእርሱ የሚቃረን መግለጫ ሰጡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሱዳን ተፋላሚ ኃይሎች በተመድ ስብሰባ እርስ በእርሱ የሚቃረን መግለጫ ሰጥተዋል።

የሁለቱ ተፋላሚ ኃይሎች መሪዎች አንደኛው ከመድረክ እና ሌላኛው ደግሞ ካልታወቀ ቦታ በመሆን በስብሰባው ላይ መግለጫ መስጠታቸውን ሮይተርስ ዘግቧል።

የሱዳን ጦር መሪ አል ቡርሃን አለምአቀፉ ማህበረሰብ ፈጥኖ ደራሽ ኃይሎችን በሽብርተኝነት እንዲፈርጅ እና ከሱዳን ድንበር ውጭ ላሉት አጋሮቹ አጸፋ ምላሽ እንዲሰጥ ጠይቀዋል።

የፈጥኖ ደራሽ ኃይሎች መሪ መሀመድ ሀምዳን ደጋሎ ወይም ሄሚቲ ባሰሙት የቪዲዮ መልእክት ለተኩስ አቁም እና ለአካታች የፖለቲካ ንግግር ዝግጁ መሆናቸውን ተናግዋል። ተፋላሚዎቹ በሀገሪቱ ዋና ከተማ ተቀስቅሶ ወደ ሌሎች አካባቢ የተስፋፋውን ጦርነት በመጀመር አንዳቸው ሌላኛቸውን ሲከሱ ተደምጠዋል።

ሄሜቲ አል ቡርሃን ከመናገራቸው በፊት ባሰሙት የቪዲዮ የሱዳን ብሄራዊ ሰንደቅ አላማ ከኋላቸው በማድረግ መግለጫቸውን አንብበዋል። ለሶስት አስርት አመታት የመሩት አል በሽር በህዝባዊ አመጽ ከወደቁ በኋላ ፈጥኖ ደራሽ ኃይሉን ወደ ብሄራዊ ጦሩ ለመቀላቀል የታያዘው እቅድ ለጦርነቱ መጀመር ምክንያት ሆኗል።

ጦርነቱ ምክንያቱ አምስት ሚሊዮን ሰዎችን አፈናቅሏል።

### የጊኒው ወታደራዊ መሪ ምዕራባዊያንን “እናስተምራችሁ ማስታችሁን አቁሙ” ሲሉ ወቀሱ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**


የጊኒው ወታደራዊ መሪ ምዕራባዊያንን “እናስተምራችሁ ማለታችሁን አቁሙ” ሲሉ ወቀሱ።

ከሁለት ዓመት በፊት በጊኒ ስልጣን በኃይል የተቆጣጠሩት ኮለኔል ማማዲ ዶምቢያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እያካሄደ ባለው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ንግግር ካደረጉ መሪዎች መካከል አንዱ ናቸው።

ምዕራብ አፍሪካዊቷ ጊኒ ወደ መጥፎ ሁኔታ እየገባች እያለ በወቅቱ በስልጣን ላይ የነበሩትን ፕሬዚዳንት አልፋ ኮንዴን በኃይል ከስልጣን በማስወገድ ታድጌያለሁ ሲሉም ተናግረዋል። ወታደራዊ የጊኒ መሪው አክለውም ምዕራባዊያን አፍሪካን እናስተምራችሁ ማለታቸውን እንዲያ ቆሙም አስጠንቅቀዋል።

የምዕራባዊያን የዲሞክራሲ ሞዴል በአፍሪካ በኃይል የተጫነ ነው ያሉት ኮለኔል ማማዱ አፍሪካ ከምዕራባዊያን በተጫነባት የዲሞክራሲ ሞዴል እየተሰቃየች እንደሆነም ተናግረዋል። አሁን ወቅቱ ምዕራባዊያን አፍሪካን እንደ ሕፃን እናስተምራችሁ የሚል እይታቸውን የሚያቆሙበት ወቅት መሆኑንም ተናግረዋል።

ኮለኔል ማማዲ በጊኒ በመፈጸሙት መፈንቅለ መንግሥት ምክንያት ከምዕራብ አፍሪካ የኢኮኖሚ



ማህበረሰብ እና አፍሪካ ህብረት አባልነት ታግዳለች። በአፍሪካ ባለፉት ሁለት ዓመታት ስምንት መፈንቅለ መንግሥት የተፈጸሙ ሲሆን ሰባቱ የተሳኩ ሆነው ስልጣን በኃይል መቆጣጠር ችለዋል።


ማሊ፣ ቡርኪናፋሶ፣ ቻድ፣ ሱዳን፣ ኒጀር፣ ጊኒ እና ጋቦን የተሳካ መፈንቅለ መንግሥት የተፈጸመባቸው ሀገራት ናቸው ሲል የዘገበው አል ዓይን ኒውስ ነው።

ማህበራዊ

# መጋቢ አዕምሮ

# ስለኢትዮጵያ

ግርማ መንግሥቴ




አሁን አሁን "ስለኢትዮጵያ" ለጆሮ እንግዳ የሆነ ርእሰ ጉዳይ አይደለም። ከአንድ ዓመት በላይን አስቆጥሮ ሁለተኛውን ጀምሮታልና ከብዙዎቻችን ጋር ትውውቅ አለው።

በግልፅ እንደሚታየው "ስለኢትዮጵያ" ከስያሜው ጀምሮ ብዙ የታሰበበት፣ ብዙም የተለፋበት። ራዕይ፣ ግብ . . . ያለው፤ በትክክል ወቅቱን ያገናዘበ (ዘግይቷል ካልተባለ በስተቀር) ከአንድ ተቋም የመነጨ፤ ግን ደግሞ በይዘቱ ሀገራዊ የሆነ ግዙፍ ሥራ ነው።

"ስለኢትዮጵያ" ኢትዮጵያ ተኮር እንደ መሆኑ መጠን ከስያሜው ጀምሮ (ስሜት ፈንቃይነቱ የባህርይው ነው እንኳን ብንል) መሰረቱ ኢትዮጵያዊ፤ መደላድሉም ማህበረ-ባህላዊ እሳቤ ነው። ስለእመብርሃን፤ ስለእግዚአብሔር፣ ስለገብርኤል፣ በኣላህ... እንዲሉ የሃይማኖት አባቶችና ምእመን፤ "ስለኢትዮጵያ"ም ተማፅኖው ይህንኑ ባህላዊ (ባህል፣ በአንድ በኩል ቁሳዊና ነባራዊ፣ በሌላ በኩል መንፈሳዊ፣ ህሊናዊ፣ ማህበራዊና የግል የፈጠራ ጥረት ገፅታዎችን የሚያካትት ሲሆን፤ ኃይማኖት በባህል ውስጥ ያለ አንድ ግዙፍ ማህበረ-ባህላዊ እሴት መሆኑን ልብ ይሏል) እሴት የተንተራሰና በዚሁ እሴት ምት፣ ቅላፄና ተማፅኖ አገርን ማሻገር ላይ ያተኮረ ተማፅኖና ምልጃ... ነው።

"ስለኢትዮጵያ" ኢትዮጵያዊ ለሆነ ሁሉ ሃይል ሰጪ፣ ብርታት ለጋሽ፣ ሞራል ገንቢና ማግኔቲክ የሆነ ጥልቅ ጽንሰ-ሃሳብ ነው።

እርግጥ ነው። "ስለኢትዮጵያ" የአንድ ትልቅና ታስቦበት ወደ ሥራ የተገባበት ፕሮጀክት ስያሜ ነው። "ስያሜ" እንበለው እንጂ ከስያሜው ጀርባ ጥሪ አለ፤ ከጥሪው ጀርባ "እባካችሁ፤ ስለ ኢትዮጵያ ብላችሁ" አለበት። ከእባካችሁ ጀርባ የትብብር፣ የአብሮነት፣ የፍቅር፣ የመተሳሰብ፣ የልማት፣ የተስፋ፣ የሠላም፣ የወንድማማችነት፣ የታሪካዊና ሥነልቦናዊ ጉዳዮች ሁሉ በአንድ ቋጠሮ አንድ ማህፀን ውስጥ የሚገኙበት ነው። ወቅታዊና ታሪካዊ ሁነቶችና ኩነቶች በአንድ የተሰናሰሉበት ነው - "ስለኢትዮጵያ"።

"ስለኢትዮጵያ" በፎቶግራፍ ኤግዚቢሽን፣ በፓናል ውይይቶችና ምሁራዊ ዲስኮሮች ይታጀብ እንጂ፣ ከሁሉም በላይ በ"የአንድነት አስተምህሮት" ላይ መልህቁን የጣለ ስለመሆኑ በሥርዓተ-ነጥብ ካልታጠረ (ሃሳቡ ካልተዘጋ፣ ለውይይት፣ ንግግር፣ ለተጨማሪ አስተያየት ክፍት ከሆነው - - -) ስያሜው የበለጠ የሚናገር ማንም የለም። ከምክንያትና ምክንያታዊነት ጋር በእጅጉ ቁርኘት ያለውና በሰዋሰው ክፍሉ "አያያዥ" ከሆነው "ስለ—" በላይ ሌላ ማስረጃ ማምጣት ትርፉ ዘጥ ዘጥ እንጂ ሌላ አይሆንም።

"ስለኢትዮጵያ" ዜጎችን ብቻ ያማከለ አይደለም። "ስለኢትዮጵያ" ኢትዮጵያን የሚሉ ሁሉ ስለ እሷ ብለው (እሷን ምክንያት አድርገው) ወደ አንድ እንዲመጡ፤ በጠረጴዛ ዙሪያ እንዲሰባሰቡ፤ ጠመንጃን "ደህና ሁን" ብለው እንዲሰናበቱ፤ ለውይይት እጅ እንዲሰጡ፤ ለዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ፤ ስለሀገራቸው፣ ሕዝብና ወገናቸው ሲሉ ሁሉም ወገኖች የዘንባባ ዝንጣፊን በመያዝ ይቅር ለእግዚአብሔር እንዲባባሉ፤ እጅ ለእጅ እንዲያያዙ፤ ለሀገረ-መንግሥትም ሆነ ብሔረ-መንግሥት ግንባታው (ዝቅ ብለን እናያቸዋለን) ሥራ ያላቸውን እንዲወረውሩ (ደበበ ሰይፉ "በትን ያሻራህን ዘር / ይዘኸው እንዳትቀበር" እንዳለው) ... "እባካችሁ!!!" በማለት ጮኸ ብሎ የሚጣራ ሀገር በቀል እሳቤ ነው።

ኢትዮጵያ ጃንጥላዋ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምእራብ እስከ ምስራቅ፣ ከጫፍ እስከ ጫፍ የተዘረጋ እንደመሆኗ ሁሉ፣ "ስለኢትዮጵያ"ም ከተማና ገጠር፣ መሀልና ዳር በሚል የተቀነበበ አይደለም። ሁሉንም ስፍራዎች፣ ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያዊያን፣ አፍቃሬ ኢትዮጵያን፣ የኢትዮጵያ ወዳጆችን፣ የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል፣ ይመለከተናል - - - የሚሉትን ሁሉ የሚመለከት፤ በዱር በገደሉ፣ በጫካ በምሽጉ - - - ያሉትን ሁሉ "ስለኢትዮጵያ" በማለት የሚማፀን መርሀ ግብር ነው። በመሆኑም፣ እድሜ፣ ፆታ፣ ሃይማኖት፣ ብሔር ብሎ ጣጣ የ"ስለኢትዮጵያ" ጉዳይ አይደሉምና ጥሪው "ሁላችሁም ተጋብዛችኋል" አይነት ነው።

"ስለኢትዮጵያ" ሃሳብ ነው፤ ለሀገርና ሕዝብ የሚጠቅሙ፣ ወንዝ የሚያሻግሩ፣ የአፈሙዝ ላንቃን የሚያዘጉ፣ አብሮነትን የሚያጠናክሩ፣ ታሪክን የሚነግሩ ... ሃሳቦች፤ የኢትዮጵያዊነት ምስጢር አቁማዳ ነው።

"ኢትዮጵያ ሲባል ማን ዝም ይላል ሰምቶ" እንዲል ቴዎድሮስ ካሳሁን፣ "ስለኢትዮጵያ" ሲታሰብም ሆነ ሀሳቡ ሲፀነስ፣ ወደ ተግባርም ሲወርድ "ማን ዝም ይላል ሰምቶ"ን ታሳቢ አላደረገም ማለት ባይቻል እንኳን፣ በኢትዮጵያዊያን ጥግ ድረስ የመተማመን ሁኔታዎች ስለመኖራቸው ምንም ጥርጥር የለም።

"ስለኢትዮጵያ" በኢትዮጵያ ጨክኖ "ወግድ" የሚል አካል እንደማይኖር የሚተማመን መድረክ እንደ መሆኑ መጠን፣ በውስጡ "ኢትዮጵያ ትቅደም!!!" (መርህ ነው)፣ "ይቻላል!!!"፣ "እናት ሀገር" ...የሚሉ አሰባሳቢ መሰረተ ሃሳቦችን የቋጠረ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል። (በነገራችን ላይ፣ "ኢትዮጵያ ትቅደም!!!" የሚለው መርህ ዝም ብሎ የተነገረ፣ ድንገት መጥ ሃሳብ አለመሆኑንና ምን ያህል እንደተደከመበት፣ በስንትና ስንት ምሁራዊ ጥናቶች፣ ደንብና መመሪያዎች እንደተደገፈ ወዘተ የቀድሞው ከፍተኛ የሥራ ኃላፊ ብርሀኑ ባይህን መጽሐፍ በማንበብ መረዳት ጥሩ ሲሆን፤ "ስለኢትዮጵያ"ም ምን ያህል ተደክሞበት እንደሆነ ወደፊት ይነገረናል ብለን እናምናለን።)

"ስለኢትዮጵያ"ን ስናጠይቅ (ጀስቲፋይ ስናደርገው) ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ ብቻ ሳይሆን፣ እሳቤያዊ ማዕቀፍ (conceptual Framework) ሆኖም ነው የምናገኘው። በመሆኑም፣ ስላለንበት አጠቃላይ ሁኔታና ይዞታ "መላምታዊ" ምላሽን ይሰጣል። ስለ ወደ ፊቱ የእኛና ሀገራችንን ጉዞ በተመለከተ ጥቁምታዎች አሉት። እንደ ሀገር ከገባንበት አዘቅት መውጫ መንገዱ ምን እንደሆነ ያመላክታል። "ሀገር"፣ "ሕዝብ" እና መሰል ቁልፍ እሳቤዎችን ቆም ብለን እንድናስብ ብቻ ሳይሆን ልናደርጋቸው ስለሚገቡን ተግባራት "መላምታዊ" አቅጣጫን ይሰጠናል። ኢትዮጵያን የሚጎዱ ነገሮች መኖር እንደሌለባቸው ያሰርፃል። ነገሩ ሁሉ "በኢትዮጵያ የመጣ በዐይኔ የመጣ ..." አይነት ነው።

ስለእመብርሃን (ሎሬት ፀጋዬ "ምነው እሙብርሃን ቀኝ እጅሽን እረሳሻት" እንዳለው ቢሆንም/ባይሆንም)፣ ስለማርያም (ምኒልክ "ማርያምን አልምርህም" እንዳሉት ቢሆንም/ባይሆንም - የሀገር ጉዳይ እዚህ ድረስ መሄዱን ልብ ይሏል)፣ በአላህ ... እንደምንለው ሁሉ፣ "ስለኢትዮጵያ" ሀገርን ስለመውደድ የሚያቀነቅን፣ አገራችንን እንድንወድ የሚማፀን፣ "ሀገሬን እወዳለሁ" የሚል ማንኛውም ሰው እውነተኛ ሀገር ወዳድነቱ የሚለካበት ስነ-ልቦናዊ ውቅርን (ሚዛንም ልንለው እንችላለን) መሰረት ያደረገ እሳቤ ነው። ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለሚወዳት ሀገሩ የጊዜ፣ የጉልበት፣ የእውቀት፣ ካስፈለገም የሕይወት መስዋእትነት እንዲከፍል የሚጋብዝ "የእናት ሀገር ጥሪ" አይደለም ካልን (ምናልባት ካለን) ሌላ ምን ልንል እንደምንችል ግልፅ አይደለም። ወደ አካዳሚው ደብር እንምጣ።

በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ ግርማ "ሀገር ማለት ምን ማለት ነው??? ሀገርን መውደድ እንዴት ይገለጣል??? በሚል ርእስ ባቀረቡት ጥናታቸው ላይ እንዳሰፈሩት "ሀገርን የመውደድ መገለጫ[ዎች] ሶስት" ሲሆኑ፤ "አንደኛው ሀገሪቱን ለማወቅ በመጣር፤ ሁለተኛው ለሀገሩ ግንባታ በሚበጁ ተግባራት ላይ በመሰማራት ሀገሩን የራሱ ለማድረግ መጣር፤ ሦስተኛው ሀገሩን ለማቆየት በሚከፍለው መስዋዕትነት ነው።"

ረ/ፕ/ር ሀብታሙ በዚሁ ጥናታቸው "ኢትዮጵያን መውደድ ማለት ምን ማለት ነው? መገለጫውስ ምንድ ነው??? በሚለው ንኡስ ርእስ ስርም "ሀገሬን እወዳለሁ የሚል ሀገሩን ስለመውደዱ የሚገልጽ ከቃላት (ከዘፈን) ባለፈ ተጨባጭ ነገር ሲተገብር መታየት አለበት፤ ሀገርን ማወቅ ሲባል ቢያንስ የሚከተሉትን ሦስት ጉዳዮችን ለማወቅና ለመመርመር መጣር ማለት ነው። አንደኛው ሀገር የምንለው ጽንሰ ሃሳብ ምን ማለት እንደሆነ፣ በዚህም ኢትዮጵያን እንደ ሀገር መረዳት፤ ሁለተኛው ሀገር ሀብት መሆኑን መገንዘብ፤ ሦስተኛው የሀገርን (የኢትዮጵያን) ሥነ-ሕዝባዊ እና ሥነ-መንግሥታዊ ታሪክን በአግባቡ በመረዳት ሀገሪቱን ለማስቀጠል የሚያስፈልገውን መረዳት እና/ወይም ዋጋ መክፈል መቻል ነው።" ማለታቸውንም ሳይጠቅሱና ከ"ስለኢትዮጵያ" ጋር ያለውን ቅን ተዛምዶ ሳያስታውሱ ማለፍ አይቻልም።

በ"ስለኢትዮጵያ" ውስጥ ያለችው ኢትዮጵያ ያው ሀገር ነችና አጥኚው በዚሁ በሴፕቴምበር 2021 ጥናታቸው "ሀገር" የሚለውን ጽንሰ ሃሳብም "ሕዝቦች የጋራ ጥቅሞቻቸውንና የሚጋጩ ፍላጎቶቻቸውን ለማስጠበቅ በአንድ መንግሥት ስር ለመተዳደር የሚገቡት ቃልኪዳን ነው፤ በመሆኑም ሀገር በሚለው ጽንሰ ሃሳብ ውስጥ ሕዝቦች (ዜጎች)፣ መንግሥት፣ የተለያዩ ተፎካካሪ እና/ወይም የሚጋሩት ፍላጎቶች ያላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች፣ እነዚሁ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች እንደ አንድ ሀገር ሕዝብ ሆነው በጋራ ለመተዳደር መነሻ ወይም መሰረት የሚሆናቸው የጋራ ጉዳይ፤ ይህን የጋራ ጉዳይ የሆነውን በአንድነት የመኖር አጀንዳ ሊያሳኩበት የሚችሉበት መንገድ (ሂደት)፤ እንዲሁም እነዚህ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች በአንድነት ለመኖር እንዲችሉ በጋራ የሚስማሙበት የጥቅም እና ግዴታ የውል ስምምነት ሰነድ ናቸው። ስለሆነም ሀገር በሚለው ጽንሰ ሃሳብ ውስጥ ሀገረ-መንግሥት፣ ሕገ-መንግሥት፣ የፖለቲካ ልሂቃን እና ብሔረ-መንግሥት የሚባሉ ጉዳዮች አሉ። በመሆኑም ሀገር ስለሚባለው ነገር የሚኖረን ዕውቀት እነዚህን ጉዳዮች ማወቅ ነው።" በማለት ያሰፈሩትን ስንጠቅስ ሃሳቡ የ"ስለኢትዮጵያ"ን ከፍታ ያሳይልናል ከሚል ጉጉት በመሆኑ አጥኚውን አመስግነን ወደ ሌላው እንሂድ። ከዛ በፊት ግን፣ አንድ ለመንገድ እንዲሉ፤

በአንድ ሀገር የሚኖሩ የተለያዩ ፖለቲካዊ ፍላጎት ያላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ፖለቲካዊ ልዩነቶቻቸውን በጎን አድርገው፣ ነገር ግን የጋራ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ተግባራትን የሚከውን አካል ሀገረ-መንግሥት ይባላል፤ ሀገረ-መንግሥቱ ይህን የሕዝቦች የጋራ ጥቅም የማስጠበቅ ኃላፊነቱ በዝቅተኛ ደረጃ ሊከውን የሚገባው ተግባር ሲሆን፣ ዋነኛ ተግባሩ ብሔረ-መንግሥት ለመመስረት ለሚደረጉ ሂደቶች መሰረት የሆኑ ተግባራትን ማካሄድ ነው፤ ይህም የተራራቁ የፖለቲካ ፍላጎቶችን ለማቀራረብ የሚስችሉ ሕገ-መንግሥታዊ፣ ተቋማዊ እና አስተዳደራዊ መሰረተ-ልማቶችን (Soft infrastructures) መገንባት ነው፤ በመሆኑም የሀገረ-መንግሥት አስፈላጊነት የተለያየ የፖለቲካ ፍላጎት ያላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ወደፊት በጋራ አብረው መኖራቸው ጥቅም እንዳለው ማሳየት፣ የአብሮነታቸው ዋስትና እንዲኖር መሰረት የሚሆነውን የጋራ ኑሮ መመስረቻ የውል ሂደትን ማስተባበር፤ በጋራ የተስማሙበትን የቃልኪዳን ሰነድ ውሎች ሳይሸራረፉ እንዲከበሩ የማድረግ ኃላፊነት ያለበት ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም ማድረግ ነው። (ዘኒከማሁ)

ከአካዳሚው ዓለም እንውጣና ወደ ራሳችን እንመለስ።

የሚመለከታቸውና የጉዳዩ ባለቤቶች ሲናገሩ እንደ ተሰማው "ስለኢትዮጵያ"ን የሚገድብ ድንበርም ሆነ ቀዩ የለም። በሁሉም ክልሎች እኩል መስተንግዶ የሚደረግለት፣ በሁሉም አካላት እኩል ተሳትፎ እየተጠናከረ የሚሄድ፤ ሁሉንም "ስለኢትዮጵያ" ስትሉ ኑ አብረን እንሁን፣ ኑ አብረን እንስራ፣ ኑ አብረን እንምከር፣ ኑ እንወያይ፣ ኑ ችግሮቻችንን እኛው እንፍታ፣ ኑ ... የሚል ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያንን ማእከል ያደረገ ሰፊ መድረክ ነው። (ከእሳቤው "እባካችሁ፣ ስለኢትዮጵያ ብላችሁ ስሙኝ፤ አንዴ አዳምጡኝ፤ እርዱኝ፤ ደግፉኝ፤ እጅ ለእጅ ተያያዙ (እንያያዝ)"፤ ይህችን ታሪካዊት ሀገራችንን አናስቀይማት ወዘተርፈ የሚሉ ድምፆች አይሰሙም? ወይም፣ "ስለእማምላክ፣ ስለእግእዚትነ ማርያም፣ ስለአላህ ... እያለ(ች)ና እጁ(ጇ)ን እያርገበገበ(ች) የሚ(ምት)ለምን ሰው አይ(ት)ታያችሁም? እነዚህ ምናባዊ ድርጊቶች ካልተሰሙና ካልታዩ የዚህ ጸሐፊ ጆሮና ዐይን "አደጋ" ላይ ነው ማለት ነው።)

እውነት ነው፣ የተለያዩ ሀገራት የተለያዩ ችግሮች ሲገጥሟቸው ነው የኖሩት። ከችግሮቻቸው ለመውጣትም የተለያዩ ብልሀቶችን መጠቀማቸውም እንደዚሁ የታወቀ ነው። በአሁኑ ሰአት ለገጠመን መከራም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት (ኢፕድ) "ስለኢትዮጵያ" ብሎ ሲነሳ፣ ሲማፀን ከችግሮቻችን መውጫ መንገድ ይሆነን ዘንድ በማሰብ ነውና ሁላችንም ለሁላችንም የወንድ በር ልንሰጥና መውጫ መንገዱን አስተማማኝ ልናደርግ ይገባል።

ፈረስ ያደርሳል እንጂ ... እንደሚባለው ፕሬስ ድርጅት እድሉን ይፈጥራል፣ መድረኩን ያመቻቻል እንጂ ስራው የዜጎች ሁሉ ነው። ኃላፊነቱ የእያንዳንዳችን ነው። "ደህና ሁን ጠመንጃ" (አገላለፁም ሆነ ሃሳቡ የፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ነው) ማለት ወይም አለማለት የሁላችንም ፋንታ ነው። ለሚቀጥለው ትውልድ ማሰብ ወይም አለማሰብ የማንኛችንም ጉዳይ ነው። ሀገርና ትውልድን የማስቀጠሉ መሰረታዊ ተግባርም እንደዛው። በመሆኑም መድረኩን ፍሬያማ ማድረግ የሁሉም ግዴታ ይሆናል ማለት ነው። ካልሆነ "ስለኢትዮጵያ" የሁላችንም ቋንቋ አልሆነም ማለት ነው። ያ ደግሞ ወደ ኋላ እንጂ ወደ ፊት ስለማያራምድ እዳው ገብስ አይደለም።

6 ታህሳስ 2019 (እአአ) ቢቢሲ "ሃምሳ የሚሆኑ ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች የተወጣጡና በኢትዮጵያ የወደፊት እጣ ፈንታ ላይ ሚና ይኖራቸዋል የተባሉ ፖለቲከኞች፣ ምሁራን፣ አክቲቪስቶች፣ ጋዜጠኞችና ሌሎችም ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ ለ11 ቀናት አብረው ውለው፣ 8 ቀን አብረው አድረው ስለኢትዮጵያ የወደፊት እጣ ፈንታ መክረዋል።" በማለት ዜና አስነብቦ ነበር። የእነዚህ ውጤቱ የት እንደደረሰ ለጊዜው ግልፅ ባይሆንም፣ የኢፕድን "ስለኢትዮጵያ" ከዚህ የሚለየው ሁሉንም በያሉበት እየሄደ፣ በየተገኙበት እየተገኘ አብሮ መምከሩ፣ እንዲመክሩም እድሉን እያመቻቸ መቀጠሉ፤ ዙሩንም እያከረረ መሄዱ ነው የሚሉ ብዙዎች ናቸው።

ወደ ማጠናቀቂያችን ከመሄዳችን በፊት፤ ስለእመብርሃን፣ በአላህ ... ስነልቦናዊ እንደመሆናቸው መጠን የ"ስለኢትዮጵያ" ማጠየቂያም በተመሳሳይ ስነልቦናዊ ነው። በቁጥር አይለካም፤ በሚዛን አይመዘንም፤ በቁና አይሰፈርም ... በ"ስለኢትዮጵያ" ባዩ (ተማፃኙ)ና ተቀባዩ መካከል ያለው ግንኙነት ስነልቦናዊ እንደመሆኑ መጠን ለስኬታማነት የሁለቱን እኩል መረዳትና መረዳዳት ይጠይቃል። ተማፃኙ "መቸም ስለ ኢትዮጵያ ብዬ እሚያልፈኝ ኢትዮጵያዊ የለም" የሚል መተማመኛም ያለው ይመስላልና አሁንም "ማን ዝም ይላል ሰምቶ"ን እዚህም እናስታውስ ዘንድ ግድ ይለናል።

በመጨረሻም፣ አንድ ለእናቱ የሆነው ጥላሁን ገሠሠ "ሁሉም ባገር ነው" እንዳለው ሁሉ፣ ሌሎችም በየመስካቸው እንዳረጋገጡት ሁሉ፣ እኛም በሕይወት ልምድም ሆነ አብሮ መኖር እንዳረጋገጥነው ሁሉ .... ነግዶ ማትረፍ በሀገር ነው። ሰርቶ ማደር፤ ዘርቶ መቃም፣ ወልዶ መሳም በአገር ነው። አንገትን ቀና አድርጎ መሄድ በሀገር ነው፤ ጸቡም ፍቅሩም የሚያምረው በሀገርና በሀገር መሬት ላይ ነው። በመሆኑም፣ የ"ስለኢትዮጵያ" መድረክ ወቅታዊና አስፈላጊያችን ነው ስንል በምክንያት ነው።

**ስለኢትዮጵያ ዝም አንልም!!!**



በአዲሱ ዓመት
ሸክ ብለናል
ስፔሻል ይሁንልን
5.5% የደስደስ ነው
በደሌ ስፔሻል
ALC. 5.5 VOL.
ሁለት አይነት ጌሾ
GOLD LABEL
BEDELE SPECIAL
PREMIUM BEER OF ETHIOPIA
EXPORT QUALITY
21+

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

# የዓባይ ግድብ የከፍታ ሳይ ከፍታዎች

**በኃይሉ አበራ**



የዓባይ ግድብ ግንባታ ብዙ ፈተናዎች አልፎ እነሆ በየጊዜው የምስራች ማሰማቱን ቀጥሏል። ባለፉት አመታት የግድቡን ሦስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት ዜና ሰምተናል፤ በ2014 ዓ.ም ሚያዝያ ወር ላይ ደግሞ በአንድ ተርባይን ኃይል ማመንጨት በመጀመሩ ብርሃን ለመሆን መንደርደሩን ተመልክተናል፤ ሌላው ተርባይንም እንዲሁ ወደ ኃይል አመንጪነት ተሸጋግሮ ብርሃን የመሆን የመጨረሻ ህልሙን በድልብስራቱ አብስሮናል። በቅርቡም አራተኛው ዙር የውሃ ሙሌት በስኬት መጠናቀቅ እንደቻለ ተመልክተናል።

መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም በአምስት ቢሊዮን ዶላር (80 ቢሊዮን ብር) የተጀመረው የዓባይ ግድብ ፕሮጀክትን ለማጠናቀቅ የተያዘለት የጊዜ መርሐ ግብርም አምስት አመት እንደነበር ይታወሳል። የግድቡ የግንባታ ሂደትም በርካታ ፈተናዎችን በማለፍ አስራ ሁለት አመታትን አስቆጥሯል። ይሁንና ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ከአምስት ዓመታት ወዲህ ግንባታው እየተፋጠነ ይገኛል። በመሆኑም ግድቡ ከከፍታው ማማ ከፍ ብሎ መታየት ችሏል። በቅርቡም አራተኛው ዙር የውሃ ሙሌት ተጠናቅቋል። ግድቡ የያዘው የውሃ መጠንም ከ42 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ በላይ ነው።

በኢትዮጵያውያንና መንግሥታቸው አንጡራ ሀብት የሚገነባውና ለታለመለት ዓላማ መዋል የጀመረው ይህ የዓባይ ግድብ ከአፍሪካም ከዓለምም ግዙፍ ፕሮጀክቶች አንዱ ከመሆኑም በላይ የኢትዮጵያውያን እንዲሁም የመንግሥታቸው ራእይ ውጤት በመሆኑ ኢትዮጵያውያን በሙሉ እንደ ዓይናቸው ብሌን ይሳሱለታል።

በአዲስ አመት ዋዜማ አራተኛውን የውሃ ሙሌት ምክንያት በማድረግ ግድቡ በሚገኝበት ስፍራ አንድ ሁነት መካሄዱ ይታወሳል። የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ጨምሮ የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች በተገኙበት በዚህ ሁነት ላይ የዓባይ ግድብ ወግ ተካሂዷል።

በመድረኩ ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ግድቡ የደረሰበትን ደረጃ፣ የታለፉ ፈተናዎችን፣ በርካታ ትርጉሞች ያሉት መሆኑን አብራርተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ 42 ቢሊዮን ሜትሪክ ኪዩብ ውሃ መያዙ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጥሮ ያሉ ጣና፣ አብጃታ፣ ላንጋኖ፣ ሻላን ጨምሮ ሁሉም ሐይቆች ተደምረው አሁን ያላቸው አቅም 70 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ነው። እስካሁን በሀገራችን ትልቁ ሐይቅ ጣና ነበር። አንድ ሰው ሰራሽ ግድብ በተፈጥሮ ኢትዮጵያ እስካሁን ያሏትን ሐይቆች በሙሉ የሚበልጥ የውሃ ክምችት ያለው ሆኖ ይታያል። ከጣና አኳያም ሲታይ ጣና 33 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ ይይዛል። የሕዳሴ ግድቡ አሁን በደረሰበት 42 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ የመያዝ አቅም፣ ከጣና በ9 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ይበልጣል። በሚቀጥለው ዓመት ደግሞ ጣናን እጥፍ ይሆናል። ይህም ሰው በእውቀቱ በገንዘቡ በአቅሙ ሁሉ ቢተባበር ምን ሊያደርግ እንደሚችል የሚያመላከት ነው በማለት አብራርተዋል።

‹‹ግድቡ ከፍተኛ አቅም ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመነጭ በመሆኑም ለኃይል ምንጭ፤ ለቤት ውስጥ ሥራ፤ ኢንዱስትሪ ለማስፋፋት ጉልህ ፋይዳ አለው›› ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የኃይል ምንጭ ብቻም ሳይሆን አካባቢን የማይበክል ንጹህና ታዳሽ የኃይል ምንጭ መሆኑን ጭምር አንስተዋል።

ዓለም ላይ በርካታ ኢንዱስትሪዎች የኢነርጂ ምንጫቸው ንጹህ ባለመሆኑ የተነሳ ከአካባቢ ጋር ተያይዞ በርካታ ክሶች እና ወቀሳዎች የሚነሱባቸው መሆኑን አመላክተው፤ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግን ኃይል ከማመንጨቱ ባሻገር እነዚህን ችግሮች የሚያስቀር በመሆኑ ተፈላጊ እንደሚያደርገው ገልጸዋል።

የዓባይ ግድብ የተገነባበት አካባቢ ከዚህ ቀደም ሞቃታማ እና በረሃማነት የበዛበት እንደነበርም ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስታውሰው፣ አሁን ግን ግድቡ ውሃ መያዝ ከጀመረ ወዲህ በከፍተኛ ደረጃ አካባቢውን እያቀዘቀዘውና ንጹህ እያደረገው መሆኑን ተናግረዋል። አካባቢው ተፈጥሯዊ ውበት እንዲያገኝ ማስቻሉንም ገልጸዋል። ‹‹የዱር እንስሳት ወደ አካባቢው ይመላለሳሉ፣ የተለያዩ እፅዋቶች ያድጋሉ፣ ከኢኮ ቱሪዝም አኳያም ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንደሚኖረው አብራርተዋል።

ግድቡ የፈጠረውን የሥራ አቅም አስመልክተው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲያብራሩ፤ በግንባታው ስፍራ ከሚሠሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሠራተኞች መካከል በትንሹ 99 በመቶው ሠራተኛ ኢትዮጵያዊ እንደሆኑና አብዛኛዎቹ ሠራተኞችም ወጣቶች መሆናቸውን ነው የጠቀሱት።

ሠራተኞቹ በግድቡ ለዓመታት ያገለገሉ እና ደጋግመው እየሠሩ በተግባር መማር የቻሉና ትልቅ እውቀት የጨበጡ መሆናቸውን አመልከተው፣ ይህ አቅም መበተን የሌለበት መሆኑን ተናግረዋል። መሰል ግድቦችን በሀገራችንም ሆነ በአፍሪካ መገንባት የሚያስችል ትልቅ አቅም የተፈጠረበት አጋጣሚ እንደሆነም ተናግረዋል፤ ለሀገራችንም ለሌሎች ሀገሮችም አዳዲስ ግድቦችን ለመሥራት የሚተርፍ አቅም እንዳይበተን፣ እንዳይበላሽ መጠበቅ ይገባልም በማለት ሂደቱ ግድብ ብቻ ሳይሆን አብሮ የተፈጠረው አቅምም አለ ብለዋል።

ግድቡ በእኔ እምነት ለብዙ አፍሪካውያን ዳግም ዓድዋ ነው። የነፃነት ምልክት፣ ራስን የመቻል፣ ከልመና የመገላገል፣ የልማት፣ የብልጸግና፣ የዕድገትና የአልንበረከክም ምልክት መሆኑን ጠቅሰው፣ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለብዙዎች ትምህርት እንደሚሆነም አብራርተዋል።

የግድቡ ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ክፍሌ ሆሮ በወቅቱ ግድቡ ከዲፕሎማሲ፣ ከቱሪዝም፣ ከኢንቨስትመንት፣ ከሀብትና ከዓሣ ልማት አኳያ ያለውን ፋይዳ አብራርተዋል። እርሳቸው እንዳሉት የዋናው ግድብ አፈጻጸም 98 በመቶ ደርሷል። የሰድል ዳም ወይም የኮርቻ ግድብ ግንባታ ሙሉ በሙሉ ተጠናቅቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል። አጠቃላይ የግድቡ ግንባታ አፈጻጸም በአሁኑ ወቅት 93 በመቶ ላይ ደርሷል።

የግድቡ የውሃ ሙሌት ባለፉት ሦስት አመታት ለሦስት ጊዜ የተካሄደ ሲሆን፣ ባሳለፍነው ሳምንት ደግሞ በ2016 ዘመን መለወጫ ዋዜማ አራተኛው ሙሊት ተከናውኗል። በመጀመሪያ ዓመት ሙሊት አምስት ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ መያዝ የታቻለ ሲሆን፣ በሁለተኛው ዓመት ሙሊትም ሦስት ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር እንዲሁም በሦስተኛ ሙሊቱ ዘጠኝ ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውሃ መያዝ ተችሏል። ከሰሞኑ የተደረገው አራተኛ ዙር ሙሊት አጠቃላይ የተያዘውን የውሃ መጠን 42 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር አድርሶታል።

አጠቃላይ የግድቡ ሁኔታ ሲታይም ግድቡ 98 በመቶ ተጠናቋል ሲባል ግድቡ ግራና ቀኝ አለው፤ የመካከል አካልም አለው። የግራና ቀኙ ከ645 እስከ 635 የሚሆን ደረጃ ያለው ሲሆን ይሄንን ለማጠናቀቅም ከ9 እስከ 10 ሜትር ብቻ ይቀራል። መካከለኛው 20 ሜትር ብቻ ይቀራል።

የዛሬ ዓመት በዚህ ጊዜ የግድቡ መካከለኛው ክፍል ተጠናቅቆ እናያለን ያሉት ኢንጂነር ክፍሌ፣ ከዚህ በኋላም የሚሠራው ቀሪ ሥራ ግራና ቀኙን የሚያገናኝ ድልድይ ብቻ መሆኑንም ጠቁመዋል። ከአራት ወራት በኋላ የግድቡ ግራና ቀኝ መጨረሻ ላይ 645 ሜትር ላይ ደርሶ እናገኘዋለንም ብለዋል።

በሌላ በኩል የኤሌክትሮ ሜካኒካል ተከላዎች እየተከናወኑ እንደሆነ ጠቅሰው፣ አሁን በሁለት ዩኒት እየመነጨ ያለው በ2016 ተጨማሪ አምስት ዩኒቶችን በማስገንባት ወደ ሰባት ዩኒቶች ለማድረስ ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን ነው ያስረዱት።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር) በበኩላቸው ሰሞኑን ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ይህንኑ አረጋግጠዋል። በዓባይ ግድብ ከዚህ በፊት ወደ ሥራ ከገቡት ሁለት ተርባይኖች በተጨማሪ በ2016 ዓ.ም አምሥት ተርባይኖች የኤሌክትሪክ ኃይል እንዲያመነጩ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል። በዚህም ኃይል የሚያመነጩት ተርባይኖች ቁጥር ሰባት እንደሚደርስም ነው ያመለከቱት።

እሳቸው እንዳሉት፤ የሰባቱ ተርባይኖች ኃይል መጠን የበለስ፣ የግልገል ጊቤ አንድና ሁለት እንዲሁም የተከዜ የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ከሚሰጧቸው አማካይ አንድ ሺህ 180 ሜጋ ዋት ተመጣጣኝ ወይም የሚበልጥ ኃይልን ለማመንጨት ያስችላል።

ይሁንና ከአቀማመጡና ከውሃ ፍሰቱ አኳያ የአምስቱ ተርባይኖች ኃይል የማመንጨት አቅምን አሁን መግለጽ እንደማያስችል የገለጹት ሚኒስትሩ፤ የግድቡ ግንባታ ሲጠናቀቅ በ13ቱ ተርባይኖች አምስት ሺህ 150 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይልን ወደ ብሔራዊ የኃይል ቋት እንደሚቀላቀል ጠቁመዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ በግድቡ የሚገጠሙት ተርባይኖች በአማካይ ከ375 በላይ ሜጋ ዋት ኃይልን ያመነጫሉ ተብሎ ይጠበቃል። በቀጣዮቹ ስድስት ዓመታት የኢኮኖሚውን ፍላጎት ማሟላት የሚችል ኃይል ከውሃ፣ ከንፋስ፣ ከፀሐይ እና ከከርሰምድር እንፋሎት ለማመንጨት ታቅዷል።

በአሁኑ ወቅት በሀገር አቀፍ ደረጃ ኤሌክትሪክ የማመንጨት አቅም አምስት ሺህ 420 ሜጋ ዋት ደርሷል። ይህንን ቁጥር የሕዳሴው ግድብ እጥፍ ያደርገዋል። እዚህ ላይ የኮይሻና ሌሎች የኃይል ምንጮች ሲጨመሩበት በቀጣይ ስድስት ዓመታት የኢትዮጵያ ኃይል የማመንጨት አቅም 17 ጊጋ ዋት ይደርሳል ነው ያሉት።

የዘንድሮውን ሙሊት ልዩ የሚያደርገው ባለፉት ሦስት ዓመታት መያዝ የተቻለው 22 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ በመሆኑና በአራተኛው ዙር ሙሊት 20 ቢሊዮን ሜትር ኪዩበ ውሃ መያዝ በመቻሉ ነው። በዚህም 42 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ላይ መደረሱ ትልቅ ስኬት እንደሆነ ሚኒስትሩ አንስተው፤ ከአሁን በኋላም በዓባይ ግድብ የሚሞላው ትርፍ ውሃ የሚመጣው ከላይ በኩል ሳይሆን እኛ በሚገባ ከሠራን በኋላ ውሃውን የምንለቅበት ደረጃ ላይ ማድረስ መቻል ሌላው ስኬት ነው ብለዋል።

ግድቡ የደረሰበት ደረጃ ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት ቁመናዋ ባገኘችው ልምድ እና እውቀት 60 የሚሆኑ በርካታ ግድቦችን መሥራት እንደምትችል ያመላከተ መሆኑንም ሚኒስትሩ ጠቁመዋል።

እሳቸውም እንዳሉት፤ የግድቡ ወቅታዊ ሁኔታ በተመለከተ የሲቪል ሥራው ወይም በሲሚንቶ የሚሠራው ሥራ በግራ እና ቀኝ የግድቡ ቁመት 145 ሜትሩ ተጠናቋል። በመካከል ያለው እና አሁን ውሃ የሚፈስበት 120 ሜትር ቦታም እስከሚቀጥለው ሰኔ ወር ድረስ እንደሚጠናቀቅ ጠቁመዋል። ኮንክሪቱ ከተሞላ በኋላም ውሃው ከታች በኩል ቁጥጥር እየተደረገበት የሚወጣ መሆኑ አንድ ትልቅ ስኬት ነው ብለዋል።

የግድቡን አራተኛ ዙር ሙሌት ይፋ ባደረጉበት ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያውያን ተባብረን በመሥራታችን የዓባይ ግድብ አራተኛ ዙር ሙሌትን በስኬት አጠናቀናል። በግድቡ ሥራ በገንዘባችሁ በእውቀታችሁ በጉልበታችሁ እና በጸሎታችሁ የተሳተፋችሁ ሁሉ እንኳን ደስ አላችሁ። ይህ ኅብረት በሌሎች ጉዳዮቻችንም እንዲሁ ሊደገም ይገባል በማለት ገልጸው፤ ለግድቡ የሚደረገው ማናቸውም ድጋፍ እስከ ፍጻሜው መቀጠል እንዳለበትም አደራ በማለት ጭምር መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

የግድቡ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ፍቅርተ ታምር ከሰሞኑ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ «ቃላችንን ዳግም በማደስ ግድባችንን እናጠናቅቅ» በሚል መሪ ቃል ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከንግድ ባንክ፣ ከልማት ባንክ፣ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክና ከሌሎችም አጋር አካላት ጋር በመተባበር ለአንድ ወር የሚቆይ ሀገር አቀፍ የሀብት ማሰባሰቢያ ንቅናቄው ተጀምሯል። በዚህም ከ500 ሚሊዮን እስከ 700 ሚሊዮን ብር ለማሰባሰብ የሚሠራ መሆኑ ተጠቅሷል።

ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤቱ በሀብት ማሰባሰብ ሥራ በ2015 በጀት ዓመት እስከ ሐምሌ 30 ቀን 2015 ድረስ ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር ቦንድ እና ስጦታ እና በ8100 ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡም ተጠቁሟል። በየዓመቱ ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ለማሰባሰብ እየተሠራ መሆኑን አስታውሰው፣ በቀጣይ 2016 በጀት አመት ከአንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ ለማሰባሰብ መታቀዱን ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ ገልጸዋል።

መንግሥት እና ኅብረተሰቡ በተባበረ ክንድ መሥራታቸው ግድቡ አሁን ላለበት 93 በመቶ መደረሱንም ገልጸዋል። ባለፉት አስራ ሁለት ዓመታት የኅብረተሰቡን ተሳትፎ በማጠናከር እስከ ሐምሌ 2015 ድረስ ከ18 ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በላይ ተሰባስቧል። እንዲሁም በጉልበት፣ በእውቀት፣ በሀሳብ ጭምር በርካታ ድጋፎች መደረጋቸውን ነው የተጠቀሱት።

የግድቡ ከፍታ 145 ሜትር ሲሆን፣ ርዝመቱ ደግሞ 1800 ሜትር ነው። ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ የሚውል 74 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ የመያዝ አቅም አለው። 13 ተርባይኖች የሚገጠሙለትና በዚህም አምስት ሺ150 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመነጭ ይሆናል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከበዓላቱ የቱሪዝም ዘርፉ ፋይዳ ሀገርን ተጠቃሚ ለማድረግ!

የያዝነው መስከረም ወር ለኢትዮጵያውያን ትርጉሙ ብዙ ነው። አዲስ ዓመትን በመቀበል የተጀመረው የመስከረም ወር በአዲስ ዓመትነቱ ብዙ ተዘክሯል። ወሩ የተስፋ፣ ከጨለማው ክረምት ወደ ነፋሻማውና በጸደይ ወደ ተንቆጠቆጠው ወቅት የመሻገር ምልክትም ነው። አዲስ ዓመቱን የተስፋ ምልክቱን ችቦ በማብራት፣ ከጎመን ምንቸት ወደ ገንፎ ምንቸት አሸጋግረን እያሉ ኢትዮጵያውያን ተቀብለውታል። በደማቅ ባህላዊ አልባሳቶቻቸው ተውበው፣ በደስታ አስተናግደውታል።

ወሩ ከዚህም ባሻገር በርካታ የቱሪዝም ፋይዳዎች ያሉት የበዓላት ወር ሊሰኝ የሚችልም ነው። በርካታ ብሔር ብሔረሰቦች በዚህ በመስቀል ደመራ ወቅት አዲስ ዓመታቸውን በዚሁ ወር ያከብራሉ፤ የቀድሞው የደቡብ ክልል ቤተሰብ ለነበሩት የወላይታ፣ የጎፋ፣ የጋሞ፣ የሀዲያ፣ የከንባታ ፣ የከፊቾ ፣ወዘተ ብሔረሰቦች ይህ ወር ትልቅ ቦታ አለው። ብሔረሰቦቹ ሰሞኑን በደማቅ የበዓል አከባበር ላይ ናቸው።

በዓሉን የሚያከብሩት ደግሞ በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩት የየብሔረሰቡ አባላት ወደ ትውልድ ስፍራቸው ሀገር ቤት በመግባት ነው። በእዚህ ወቅት በእነዚህ አካባቢዎች ከፍተኛ የሕዝብ እንቅስቃሴ ይታያል፡፡

ወሩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች ዘንድም የመስቀል ደመራ በዓል የሚከበርበት እንደመሆኑ ትልቅ ስፍራ አለው። በዓሉ በአዲስ አበባና በሌሎችም ከትንሽ እስከ ትልቅ ከተሞች፣ በየመንደሩም ጭምር በአደባባይ በድምቀት ይከበራል፡፡

በኦሮሞ ብሔረሰብ ዘንድ በድምቀት የሚከበረው የኢሬቻ በዓልም ሌላው የወሩ ታላቅ በዓል ነው። ይህ በዓል በዋናነት በአዲስ አበባና ቢሾፍቱ በደማቅ ሥነ ሥርዓት የሚከበር ሲሆን፤ በየአካባቢውም በተመሳሳይ በድምቀት ለቀናት ይከበራል። ዘንድሮ ደግሞ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በደማቅ ሥነሥርዓት የሚከበረው የመውሊድ በዓልም የዚሁ የመስከረም ወር ድምቀት ሆኗል።

ሁሉም በዓላት መሰባሰብን የሚጠይቁ ናቸው፤ በግልም፣ በቤተሰብም አምሮ ተውቦ ለመገኘት ብዙ ጥረት ይደረጋል። ለዓመታት የተለያዩ የቤተሰብ አባላት ይገናኙባቸዋል፤ መደጋገፍ ጎልቶ ይታይባቸዋል። ለዚህ ደግሞ ሰፊ ዝግጅት ይደረጋል።

እነዚህ በዓላት በድምቀት ያለምንም የጸጥታና ደህንነት ችግር እንዲከበሩ፣ የትራንስፖርት ስምሪቱ የተሳለጠ እንዲሆን፣ ሕዝቡ እንደልቡ እንዲንቀሳቀስ መንግሥትና የተለያዩ አደረጃጀቶች አጥብቀው ይሠራሉ። የበዓላቱ ባለቤቶችም ከግለሰብ አንስቶ እስከ ተቋማት ድረስ በዓላቱ በሰላምና በድምቀት እንዲከበሩ አጥበቀው ይሠራሉ። ዘንድሮም ይሄው እየተደረገ ነው።

በሌሎች በዓላት ላይም ተመሳሳይ ዝግጅት እንደሚደረግ ይታሰባል። ሁሉም የየራሱ በዓል በድምቀት እንዲከበር ከሚያደርገው ርብርብ በተጓዳኝ የሌላውም በዓል በተመሳሳይ መልኩ እንዲከበር ማድረግ ላይም መሥራት ያስፈልጋል።

ይህ ሲሆን በዓላቱ በሰላም ይከበራሉ፤ ከበዓላቱ የሚጠበቁ የቱሪዝም ጥቅሞችም ይገኛሉ። የእነዚህ በዓላት የቱሪዝም ፋይዳ ከፍተኛ ነውና ከበዓልነታቸው ባሻገር ዘርፈ ብዙ ጥቅም ምንጮችም ናቸው። የበዓላቱ ብዛትና በድምቀት መከበር ሲታሰብ፣ ይህ ወቅት የኢትዮጵያ የቱሪዝም እንቅስቃሴ ጎልቶ ከሚወጣባቸው ወቅቶች አንዱ ነው ሊያሰኝ ይችላል። ከፍተኛ የሆነ የሀገር ውስጥ ቱሪስት ፍሰት የሚታይበትም ነው። በዓላቱ የውጭ ዜጎችም በብዛት የሚታደሙባቸው እንደመሆናቸው ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ቱሪስት ወደ ሀገሪቱ በመግባት ወደ ተለያዩ አካባቢዎች እንደሚንቀሳቀስ ይጠበቃል።

መላው ሕዝብ ሊባል በሚችል ደረጃ እንዲሁም የውጭ ቱሪስቶች በሚነቃነቁባቸው በእነዚህ በዓላት ወቅት ከፍተኛ ሀብትም አብሮ ይንቀሳቀሳል። ግብይቱ፣ ልገሳው፣ መገባበዙ ፣ ወዘተ ይጦፋል። ይህ ደግሞ የቱሪዝም ዘርፉን በማስተዋወቅና ማስጎብኘት ብቻ ሳይሆን በገቢም የበለጠ ሀብት መሰብሰብ እንዲቻል ትልቅ አቅም ይሆናል።

ከበዓላቱ ሀገርንም በቱሪዝም ዘርፉ ተጠቃሚ ለማድረግ በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል፤ በተለይ በባህልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚሰሩ መንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ የግሉ ዘርፍ ተቋማት እነዚህ የቱሪዝም ዘርፉን በአያሌው የሚያንቀሳቅሱ በዓላት በሚገባ እንዲከበሩ፤ እንዲሁም ተገቢው ሀብት እንዲገኝ ለማድረግ መሥራት ካለባቸው የዓመቱ ወቅቶች ይህ ወቅት አንዱ መሆኑን ተረድተው መሥራት ይኖርባቸዋል። ለሀገር ተጠቃሚነት ሌት ተቀን በመሥራት ከእዚህ የቱሪዝም አዝመራ ሀገር ተገቢውን ምርት መሰብሰብ እንድትችል መትጋት ይኖርባቸዋል።

እንደሚታወቀው መንግሥት የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ እየሠራ ነው፤ የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው የአስር ዓመት ዕቅድ ዋና ምሰሶ አድርጎ ከያዛቸው ዘርፎች አንዱ የቱሪዝሙ ዘርፍ ነው። ይህን ሲያደርግ ደግሞ ዘርፉ የሚያድግበትን መደላድል በመፍጠር ነው። ዘርፉ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤት እንዲዋቀር አድርጓል፤ ሀገሪቱ በርካታ የቱሪዝም መዳረሻዎች ቢኖሯትም፣ አዳዲስ የቱሪዝም መሠረተ ልማቶችን በግዙፍ ፕሮጀክቶቹ ቀርጾ ወደ ሥራ አስገብቷል፤ ሌሎችም ወደ ሥራ ሊገቡ በመንገድ ላይ ይገኛሉ። በቀጣይም ሌሎች ይገነባሉ። እነዚህ በሀገር ውስጥ ቱሪዝም ላይ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ፣ የውጭ ቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜ ሊያራዝሙ የሚችሉ መሰረተ ልማቶች በእነዚህ በዓላት ወቅት እንዲጎበኙ ለማድረግ መሥራት ከቱሪዝም ዘርፉ የሚጠበቀውን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ይጠቅማል።

የዓለም ቱሪዝም ቀን የሚከበረው በዚሁ በመስከረም ወር ነው፤ እነዚህ በርካታ በዓላት ለቱሪዝም ዘርፉ ትልቅ አቅም መሆናቸውን ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብም ሆነ ለኢትዮጵያውያን ማስተዋወቅ፣ ማስጎብኘትና ከዘርፉ የሚገኘውን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ተጠናክሮ መሥራት ያስፈልጋል!

**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ጠንካራ የውሃ አጠቃቀም ሕግ ያስፈልገናል

ግርማ መንግሥቴ

በየትኛውም ሚዛን እንመዘን፣ በየትኛውም መስፈርት እንለካ የውሃ አጠቃቀማችን ሕግ ቢኖር በወንጀል የሚያስጠይቅ እንደሚሆን ለመናገር የሚከብድ አይደለም። ይህንን ድፍረት የተሞላበት የሚመስል ድምዳሜ በማስረጃ ለማየት እንሞክር።

በሀገራችን ውሃን በተመለከተ ያለው እውነታ እርስ በርሱ የሚጋጭና ግራ የሚያጋባ (ፓራዶክስ) ነው። ሀገራችን እንደ ሀገር "የውሃ ማማ" ነች። የብዙ የውሃ አካላት /ወንዞች ሀይቆች /ባለቤት ነች። ይህም ሆኖ ግን ሕዝቦቿ በንጹህ ውሃ እጥረት የከፋ ችግር ውስጥ ካሉ የዓለም ሕዝቦች አንዷ ናት ።

እውነታው ግራ የሚያጋባ / አያዎ "ፓራዶክስ" ነው። ግራ አጋቢው የሀገራችንን የውሃ ማማነት ሳይሆን ማማነታችንን ወደ ተጠቃሚነት መለወጥ አለመቻላችን ነው። የውሃ ሀብታችንን በተለይም ለመጠጥ ተብሎ ብዙ ዋጋ ተከፍሎ የሚመረተውን ውሃ ለተገቢው ዓላማ በኃላፊነት ማዋል ስላለመቻላችን ነው።

"ንፁህ ውሃን ንፁህ ውሃ ለማይፈልጉ ተግባራት" በማዋል በኩል በዓለም የሚስተካከለን በጭራሽ ያለ አይመስልም። ይህም በሀገራችን ላይ ያለው የውሃ ሀብት ምን ያህል ለአደጋ እንደተጋለጠና በግዴለሽነት እየባከነ እንደሆነ የሚያሳይ ነው ።

እዚህ ላይ "ንፁህ ውሃ የማይፈልጉ" ስንል ሰውን ብቻ ንፁህ ውሃ ፈላጊ አድርገን እንዳንወስድ መጠንቀቅ አለብን፤ ሕይወት ያለው ሁሉ ንፁህ ውሃን ይፈልጋል እና ፤ የማግኘትም ሙሉ መብት አለው። እኛ ሀገር ግን በአብዛኛው የንፁህ ውሃ የሚውለው ሕይወት ላለው ፍጡር ሳይሆን ግኡዝ ለሆነ አካል የተለያየ አገልግሎት ነው።

ለምሳሌ ለመኪና እጥበት የሚውለውን ፣ ብዙ ዋጋ ተከፍሎበት ለመጠጥ የተዘጋጀውን ውሃ እንመልከት። እኛ ሀገር እኮ ይህ መኪኖች እየታጠቡ ያለው ነዋሪዎች ለማግኘት ብዙ ውጣ ውረድ በሚከፍሉበት ንፁህ የቧንቧ ውሃ ነው። በዚህ ጉዳይ ያለኝን አንድ ገጠመኝ ላካፍላችሁ።

፣ ጠዋት ከቤቴ ወደ ሥራ ስመጣ አልፌው የምመጣው አንድ ግቢ አለ። ባለቤቱ ባለ መኪና ናቸው። የ10 ዓመት አካባቢ ልጃቸው ሁሌ መኪናዋን ያጥባል። የሚያጥበው ጊቢ ውስጥ ያለው ቧንቧ ላይ ረጅም ላስቲክ አስገብቶ በላስቲኩ መኪናዋ ላይ በመርጨት ነው።

ልጁ ከአለባበሱ ጀምሮ ሥራውን እንደ መዝናኛም፣ እንደ ስፖርትም እየተጠቀመበት ስለመሆኑ ከፈገግታው ጀምሮ ሁኔታዎቹ ይናገራሉ። አሁን ችግሩ የልጁ፣ ወይም ልጁ ጋ አይደለም። ችግሩ በዚህ አይነት ኃላፊነት በጎደለው መንገድ ሲንቀሳቀስ ሀይ በል የሚለው ከልካይ ሕግ /መመሪያ አለመኖሩ ነው ። ውሃው ሁሌ ጠዋት ጠዋት ዝም ብሎ እንደ ጉድ ይፈሳል።

ከብዛቱ የተነሳ ቀጭንና ረጅም፣ በሳር የለመለመች ቦይ ሰርቷል። ሁሌም አጠገቡ ማንም ሰው የለም። አንድ ቀን (ሥራውን ካደነቅሁለት በኋላ) ውሃውን እየቆጠበ ቢጠቀም ጥሩ እንደሆነ ነገርኩት። መልስ አልሰጠኝም። እነሆ፣ ዛሬም ድረስ በገፍ እንዳፈሰሰ አለ።

የዚህን ልጅ የውሃ አባካኝነት (ውሃ የማያልቅ ሀብት ይመስል) ከሌሎች እሱን መሰሎች ጋር ተዳምሮ (በንፁህ የመጠጥ ውሃ እጥረት በቀን ከ700, 000 በላይ ሰው የሚሞትባት፤ 2.2 ቢሊዮኖች ንፁህ ውሃ የማያገኙባት ዓለማችንን ይዘን) በየቀኑ ሊባክን የሚችለውን ንፁህ የመጠጥ ውሃ መገመት ይቻላል። ያኔ፣ በመግቢያ ላይ "ሕግ ቢኖር" የተባለውን ካልደገፋችሁ ከምላሴ ፀጉር ይነቀል።

ሌላ ልጨምር ፤ አዲስ አበባ ውስጥ ከ45 በላይ ወንዞች አሉ። በአብዛኛዎቹ ወንዞች አካባቢ መኪና አጣቢዎች አሉ። ቧንቧ ላይ ደቅነው በመርጫዋ (የውሃ ወንፊቷ) እየረጩ ከማጠብ ውጪ፣ አንዳቸው እንኳን ከወንዙ እየቀዱ መኪናዎቹን ሲያጥቡ አይታችኋል? ታዲያ ይሄንን ምን ይሉታል?? ቢያንስ ቢያንስ ንፁህ የመጠጥ ውሃ ግፍ የለውም? እንዲህ እንዲህ እያላችሁ ከተሞቻችንን ብትፈትሹ (የአዲስ አበባን ዝም ነው) ንፁህ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚው ሰው ሳይሆን ምን እንደ ሆነ ትደርሱበታላችሁ።

በተመሳሳይ ወደ ኮንስትራክሽኑ ዘርፍ ደግሞ እንሂድ፤ በሀገራችን፣ በተለይም በከተሞች፣ የግንባታ (ኮንስትራክሽን) ሥራዎች በገፍ መሰራት ከጀመሩ ቢያንስ ሁለት አስርት ዓመታት ተቆጥረዋል። አንዳንዶቹ ከተሞች (ሰፈሮች) ጭራሽም ፈርሰው እየተሰሩ ነው። ሌሎቹን ሁሉ ትተን የፎቆቹንና ግዙፍ ተቋማትን ብቻ እንኳን ብናስብ፣ በኢትዮጵያ ሁኔታ የምድር አሸዋ ... በሚል ልናሰላቸው ምንም አይቀረንም። ልብ በሉ፤ ከጥቂቶች በስተቀር፣ እነዚህ ሁሉ የሚጠቀሙት ንፁህ የመጠጥ ውሃን ከቧንቧ እየቀዱ ነው። አይዘገንንም??

እንደ ሕግና ደንብ (እኛ ያለን አይመስለኝም) ቢሆን ኖሮ አንድ ባለ ሀብት ሕንፃ ሲገነባ እዛው የሚገነባበት አካባቢ የጉድጓድ ውሃ በማውጣት ነው ለግንባታ ተግባሩ ማዋል ያለበት። ወይም፣ ከአካባቢው ካለ ወንዝ ጠልፎ፤ ወይም፣ አካባቢው ላይ የተበከለ ውሃ እንኳን ካለ እሱን በመርዝ አጥርቶ ወደ ጥቅም በመቀየር ሥራ ላይ ማዋል ይጠበቅበታል እንጂ ንፁህ የመጠጥ ውሃን ከቧንቧ እየቀዳ ለግንብ አያጠጣም። በኢትዮጵያ ግን ይህ የለም፤ አይታሰብምም።

ከዚህ ሁሉ ብልሹ አጠቃቀማችን ላይ በየቤቱ፣ በየአስፋልቱ (እየፈነዳ) ... ሲፈስ የሚከርመውን ጨምሩበትና አስሉት። ያኔ በዓለም ተወዳዳሪ የሌለን የውሃ አባካኞች መሆናችንን እየዘገነናችሁም ቢሆን ትረዳላችሁ።

እዚች ጋ ዶቸ ቬለ ዓለም አቀፉ የጤና ድርጅት መረጃ ጠቅሶ እንደዘገበው፤ የኮሌራ በሽታ ከጎርጎሮሳዊው 2005 ዓ.ም ጀምሮ በድሃ ሀገሮች እየጨመረ መጥቷል። በተለይ ኢትዮጵያን በመሳሰሉ መሠረተ ልማቶች ባልተሟሉባቸው ሀገራት ከንፁህ መጠጥ ውሃ እጥረት ጋር ተያይዞ የአካባቢና የግል ንፅህናን ለመጠበቅ አስቸጋሪ በሆነባቸው ቦታዎች በሽታው የከፋ ጉዳት ያደርሳል" ይህ እንግዲህ ሌላው ተያያዥ ችግር ነው።

### የንፁህ ውሃ መጠጥ ፍላጎትና አቅርቦት

በ2018 "ወተር ኤይድ" የተባለው በጎ አድራጎት ድርጅት የንፁህ ውሃ አቀርቦት ሳይኖር፤ ከጤና፣ ከትምህርትና ከፆታ እኩልነት ጋር የተያያዙ ዓለም አቀፍ ግቦችን ማሳካት እንደማይቻል በመግለጽ፤ ፖለቲከኞች ለውሃ አቅርቦት ትኩረት እንዲሰጡ ጥሪ አቅርቦ እንደነበር ይታወሳል።

በንፁህ ውሃ አቅርቦት ችግር በቀዳሚነት ከሚጠቀሱት ሀገራት አንዷ ኢትዮጵያ እንደሆነች መረጃዎች ያመለክታሉ፤ ከአጠቃላይ ሕዝቧ 42% የሚሆነው ብቻ ንፁህ የመጠጥ ውሃ የሚያገኝ ነው። ከዚህ ውስጥ ንፅህናውን የመጠበቅ እድል ያለው 11% ያህሉ ብቻ ነው።

አዲስ አበባን እንደማሳያ ብንወስድ፤ በቀን ወደ 1ሚሊዮን 300ሺህ ሜትር ኪዩብ ያስፈልጋታል። አቅርቦቷን ስንመለከት ደግሞ 722ሺህ ሜትር ኪዩብ ሆኖ እናገኘዋለን። መስተዳድሩ በቅርቡ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በመተባበር ባሳተመው መጽሔት ላይ በ2015 ዓ.ም 186 ነጥብ 52 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ንፁህ የመጠጥ ውሃ መመረቱን አስታውቋል።

ከዚህ ውስጥ ምን ያህሉ በትክክል ሕይወት ላላቸው (ሰው፣ እንስሳትና እፅዋት) ፍጡራን ይውላል፤ ምን ያህሉስ ለግኡዛን (መኪና፣ ግንብ) እየዋለ ነው? ብለን ብንጠይቅ መልስ የሚሰጠን ያለ አይመስለኝም።

ከተግባራቱ አንዱ "የውሃ ብክነትን መቀነስ" የሆነው መሥሪያ ቤትም ፤ የአዲስ አበባ ከተማ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፤ ደረቱን ነፍቶ በአደባባይ ሊቆም የሚችል ምላሽ አለው ለማለት ያስቸግራል።

እዚህ ላይ ዛሬ በአግባቡ ልናስተውለው የሚገባው፤ውሃ አላቂ ሀብት ከመሆኑ አንጻር፤ሀብቱን ባልተገባ መልኩ በብክነት ጨርሰነው የነገው ትውልድ ለከፋ አደጋ እንዳይጋለጥ ነው። ለዚህም የሚመለከታቸው አካላት ጠንካራ የውሃ አጠቃቀም ሕግ ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል ፤እኛም ኃላፊነት እንደሚሰማው ሕዝብ ውሃ መቆጠብን ባህላችን ማድረግ ይጠበቅብናል።

# ስፖርት





# ሀገር አቀፍ የውሃ ዋና ክለቦችን ለማቋቋም ጥረት እየተደረገ ነው

ዓለማየሁ ግዛው

በኢትዮጵያ በርካታ የስፖርት ዓይነቶች ቢዘወተሩም አብዛኞቹ በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ በክለብ ደረጃ አይዘወተሩም። በኢትዮጵያ እምቅ አቅም እንዳለ በሚታመነው የውሃ ዋና ስፖርት ከእነዚህ መካከል አንዱ ነው። ክለቦች ተደራጅተው የእርስ በእርስ ውድድሮች ማድረጋቸው ለስፖርቱ ማደግና ተወዳዳሪ መሆን የሚያበረክተው አስተዋጽኦ የላቀ እንደሆነ ይታመናል። ይህንን ከግምት በማስገባትም ሀገር አቀፍ የውሃ ዋና ስፖርት ክለቦችን የመቋቋም ሃሳብን እውን ለማድረግ የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች (ኢትዮጵያን አኳቲክስ) ፌዴሬሽን ወደ እንቅስቃሴ ተገብቷል።

በኢትዮጵያ ስፖርት ፖሊሲ መሰረት አንድ ስፖርት ፌዴሬሽን ተብሎ ሊጠራ የሚችለው በአምስትና ከዚያ በላይ ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች ሲዘወተር ነው። በተመሳሳይ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ፌዴሬሽን የመሆን ህጋዊ እውቅና የሚያገኙት በትንሹ አምስት ክለቦችን ማቋቋም ሲችሉ ነው። በመሆኑም በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተጠቀሰውን ያህል ክለቦች እንደሚኖር የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን እምነት ነው።

ፌዴሬሽኑ ይህንን ለማጠናከርና የረጅም ጊዜ እቅዱ የነበረውን የክለብ ምስረታ ወደ መሬት ለማውረድ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ መድረስ



የኢትዮጵያ ውሃ ዋና ስፖርቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰረት ደምሱ፣

ችሏል። በዚህም መሰረት በፌዴሬሽን ደረጃ የክለብ ምስረታ ለማድረግ ከተለያዩ ተቋማት ጋር በሚደረገው ግንኙነት መልካም የሚባሉ ምላሾችን አግኝቷል። ክለብ በማቋቋም ወደ ተግባር መግባት የቻሉ እና በሂደት ላይ ያሉ ክለቦችም እንዳሉም ተጠቁሟል። መከላከያ እና አየር ኃይል ክለብ ለማቋቋም ወደ እንቅስቃሴ ከገቡ ተቋማት በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ። መከላከያ ክለብ ለማቋቋም ሥራ የጀመረ ሲሆን አየር ኃይል ከፌዴሬሽኑ በቀረበለት ጥያቄ መሰረት ክለብ ለማቋቋም በጎ ምላሽ መስጠት ችሏል።

የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት መሠረት ደምሱ «የአንድ ስፖርት ማደግ ዋና መሰረቱ የጠንካራ ክለቦች መኖር ነው» ሲሉ ይጠቁማሉ። በየክልሉ አምስት ክለቦች ይኖራሉ ተብሎ ቢታሰብም በተግባር ለማረጋገጥና የቁጥጥር ስራውን በአንዴ ለማጥራት ግን አስቸጋሪ ነው። ፌዴሬሽኑ የክለብ ውድድሮችን ለማድረግ ጥረት በሚያደርግበት ወቅት የሚፈለገውን ያህል ክለብ ከክልል ማግኘት ባለመቻሉም ሀገር አቀፍ ክለቦችን ለመመስረት እንዳስገደደውም ይናገራሉ። በሚፈለገው መጠንና ብቃት ክለቦች እየተሳተፉ ባለመሆናቸውም ፌዴሬሽኑ እነዚህን የክልል ክለቦች ወርዶ በተገቢው መልኩ ቁጥጥር ለማድረግ እቅድ ይዟል። ክለቦች በምንያህል ደረጃ እንደ ተጠናከሩ፣ ከሌሉም ፌዴሬሽን ለመባል ያለውን መስፈርት ማሟላታቸውን የማጣራት ሥራ ይከናወናል።

በፌዴሬሽን ደረጃ ክለብ ለማቋቋም ጠንካራ የሆነ እምነት በመኖሩ የተለያዩ ተቋማት ጋር ደብዳቤዎችን በመለዋወጥ ክለቦችን ለማቋቋም ሂደቱን የጀመሩ ተቋማት መኖራቸውንም ፕሬዚዳንቷ ያስረዳሉ። ፌዴሬሽኑ በያዘው እንቅስቃሴ በመቀጠልና በማስፋት በሀገር አቀፍ ደረጃ ጠንካራ የውሃ ዋና ክለቦች የሚመሰረቱበትን ሁኔታ በማቀድ እየሰራም ይገኛል። እነዚህን በፌዴሬሽን ደረጃ የሚቋቋሙ ክለቦች ለመመስረት ተቋማት ለስፖርቱ የሚያስፈልገውን መሰረተ ልማት ማሟላት ይኖርባቸዋል። ክለብ በሚመሰረትበት ወቅት በግል ማሟላት ባይቻልም ስፖርተኞቹን ተከራይቶ የሚያሰሩበት የውሃ ዋና ገንዳ ሊኖራቸውም ይገባል። በተጨማሪም አሰልጣኝ መቅጠርና ለስፖርተኛው ደመወዝ የሚከፍሉበት እና ለስፖርቱ የሚያስፈልገውን ቁሳቁስ ማሟላት ለክለብ ምስረታው እንደ መስፈርት መቀመጡንም ፕሬዚዳንቷ አስረድተዋል።

ክለቦቹ ከተቋቋሙ በኋላ አዲስ የውድድር ሥርዓት በመፍጠር የክለቦች ውድድር ይካሄዳል። እስከ አሁን በነበረው የውድድር ሥርዓት የክለብና የክልል ውድድር በአንድ ላይ ይከወን ነበር። በዚህና በውድድሩ አለመጠናከር ምክንያትም ክልሎቹ ለመሳተፍ ፍቃደኛ አልነበሩም። ይህም የተጠናከረ ክለብ ያለመኖሩ ዋና ማሳያ ጭምር ነው። ውድድር መስፋቱ ጥሩ ስፖርተኞችን ለማፍራትና ስፖርቱን ለማስፋት ቁልፍ ጉዳይ በመሆኑ ፌዴሬሽኑ ውድድሮችን ለማስፋት ቁርጠኛ እንደሆነም ፕሬዚዳንቷ አስረድተዋል። ሆኖም ከመሰረተ ልማትና ከፋይናንስ ጋር የተያያዙና የክልሎችና ክለቦች ፌዴሬሽኑ በሚፈልገው ልክ እንዳይሰራ ማነቆ ሊሆንበት ችሏል። በቀጣይም ከክልሎቹ ጋር በመነጋር ክለቦቹ የሚጠናከሩበትንና በሀገር አቀፍ ደረጃ ትልልቅ ክለቦች የሚቋቋሙበትን ሁኔታ በመፍጠር የሚሰሩ ይሆናል።


## ጨረታ ማስታወቂያ

ድርጅታችን ሰዎች ለሰዎች በአርሲ ዞን ሊሞና ቢልቢሎ ወረዳ (በቆጂ አካባቢ) መረሮ ከተማ ለሚያስገነባው የመረሮ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ግንባታ ፕሮጀክት መጠኑ ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ የተጠቀሰውን ጥራቱን የጠበቀ የወንዝ አሸዋ፣ ጠጠር 02ሚ.ሜ እና 01ሚ.ሜ፣ የግንብ እና የመሠሻታ ድንጋይ እና ምርጥ አፈር አቅራቢዎችን አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል።

| ተ.ቁ | የእቃው ዓይነት | መስኪያ | የሚፈለገው መጠን |
|---|---|---|---|
| 1ኛ | ጥራቱን የጠበቀ የወንዝ አሸዋ ትራንስፖርቱን ጨምሮ | ሜ. ኩብ | 555 |
| 2ኛ | ጥራቱን የጠበቀ 02 ሚ.ሜ በማሽን የተመረተ የአርማታ ጠጠር ትራንስፖርቱን ጨምሮ | ሜ. ኩብ | 343 |
| 3ኛ | ጥራቱን የጠበቀ 01ሚ.ሜ በማሽን የተመረተ የአርማታ ጠጠር ትራንስፖርቱን ጨምሮ | ሜ. ኩብ | 64 |
| 4ኛ | ጥራቱን የጠበቀ የግንብ ድንጋይ ትራንስፖርቱን ጨምሮ | ሜ. ኩብ | 424 |
| 5ኛ | ጥራቱን የጠበቀ የመሠሻታ (የሀርድኮር) ድንጋይ ትራንስፖርቱን ጨምሮ | ሜ. ኩብ | 603 |
| 6ኛ | ጥራቱን የጠበቀ ምርጥ አፈር (ሴሌክትድ ማቴሪያል) ትራንስፖርቱን ጨምሮ | ሜ. ኩብ | 200 |

**አመልካቾች፤**

1. ተጫራቾች በዘርፉ የታደሰ የንግድ ፈቃድ እና ግብር መለያ ቁጥር (Tin No.) ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።
2. ተጫራቾች የዋጋ ማቅረቢያ ኦርጅናል እና ሌሎች ሰነዶች በተራ ቁጥር 1 የተዘረዘሩትን ፎቶ ኮፒውን **በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ** ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ተከታታይ የስራ ቀናት አዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ቡልቡላ ወረዳ 12 ቀይ አፈር አካባቢ ሰዎች ለሰዎች ድርጅት ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ዋና ጽ/ቤት ወይም አሠላ በሚገኘው የሰዎች ለሰዎች ድርጅት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።
3. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ የሚያቀርቡትን ዋጋ 1% ሲፒኦ (CPO) ከዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ ጋር ማስያዝ አለባቸው፤
4. ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ለመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ተጨማሪ ማብራሪያ ካስፈለገ በስልክ ቁጥር**

አዲስ አበባ 0114 71 43 20/011471 43 58

አሠላ 0912 685997 በሥራ ሰዓት ደውሎ ማብራሪያ ማግኘት ይቻላል።

## የሰዎች ለሰዎች ድርጅት